ጁላይ 2014

# ወታደራዊ የሙያ ብቃትን ማጎልበት በአፍሪካ

በኢሚሌ ኡወድራጎ

ኤሲኤስኤስ ጥናታዊ ጽሁፍ #6



# ስትራቴጂያዊ ጥናቶች በአፍሪካ ማእከል

የስትራቴጂያዊ ጥናቶች በአፍሪካ ማእከል የሚደግፈው የዩናይትድ ስቴተስ የውጭ እና የደህንነት ፖሊሲዎችን ሲሆን ይህም የአፍሪካ ሃገሮች የደህንነት ስጋቶችን ሲቪል ና ወታደራዊ ትብብርን፣ የዲሞክራሲያዊ እሴቶች በሚያከብር መልኩ፣ እና የሰብኣዊ መብቶችን በሚጠብቅ መልኩ ለመለየት እና ለመፍታት ያላቸውን ስትራቴጂያዊ ብቃት ለማጠናከር ነው።

# ወታደራዊ የሙያ ብቃትን ማጎልበት በአፍሪካ

በኢሚሌ ኡወድራጎ

ኤሲኤስኤስ ጥናታዊ ጽሁፍ #6

ዋሽንግተን ዲሲ
ጁላይ 2014

አመለካከቶች፣ ድምዳሜዎች፣ እና ምክረ ሃሳቦች በዚህ ውስጥ ሲገለጹ የአቅራቢዎቹ ብቻ ሲሆኑ፣ የስትራቴጂያዊ ጥናቶች በአፍሪካ ማእከሉን፣ የመከላከያ ሚኒስቴሩን፣ ወይም የሌላ የፌዴራል መንግስቱን አመለካከቶች አይወክሉም።

የዚህ ስራ ክፍሎች ሊጠቀሱ ወይም ያለፍቃድ በድጋሚ ሊታተሙ ይችላሉ፤ ይህም የተለመደው ምንጩን መግለጽ እስከተካተተ ድረስ።

የመጀመሪያው ህትመት፣ ጁላይ 2014

ISSN 2164-4128 (ህትመት)
ISSN 2164-4101 (ኦንላይን)

ለስትራቴጂያዊ ጥናቶች በአፍሪካ ማእከል ተጨማሪ ህትመቶች፣ የማእከሉን ድረ ገጽ በዚህ ይጎብኙ http://africacenter.org.

# ማውጫ


ዋና ማጠቃለያ .......................................... 1

የአፍሪካ ወታደራዊ ክፍሎች ፈተናዎች ................. 3

የወታደራዊ ሙያ ክህሎት መመሪያዎች ................. 5

ዲሞክራሲያዊ ሉኣላዊ ስልጣን .................................. 5

ወገናዊነት ....................................................... 6

ስነ ምግባራዊ ተቋም ........................................... 15

የወታደራዊ ሙያ ክህሎት በአፍሪካ መሰናክሎች .......16

የቅኝ ግዛት ውርስ ................................................ 16

የብሄር እና የጎሳ መድልዎዎች .................................. 17

የወታደሩ ፖለቲካዊ ማንነት መዳበርና የፖለቲካው ወታደራዊ ስብእና መውሰድ................................................ 20

ደካማ የአሰራር ብቃት፥ አላማ የሌላቸው ወታደሮች ምልክት .. 23

የአፍሪካን ወታደሮች ክህሎቶች ለመገንባት ቅድሚያ ነገሮች ..........................................34

የወታደሩን አላማ መከለስ ........................................ 34

አላማውን እንደገና መወሰን፤ ................................ 34

ወታደሮች የሚሰሩበትን ሁኔታ ከፖለቲካ ነጻ ማድረግ .......... 39

ግብረ ገብነት እና ተጠያቂነትን ወደ ወታደሩ ባህል ተቋማዊ ማድረግ ........................................................ 44

ማጠቃለያ ..............................................49

ማስታወሻዎች .........................................51

ስለ ጸሃፊው ...........................................56

# ዋና ማጠቃለያ

በተከታታይ በአህጉሩ አለመረጋጋት በሚወጡት ዜና ዘገባዎች የአፍሪካን ደካማ ወታደራዊ የሙያ ብቃት ምሳሌዎችን ማየት ይቻላል፡፡ ወታደራዊ ሃይል ባልተደራጁ ታጣቂ ሃይሎች መፈረካከስ፣ መፈንቅለ መንግስት፣ ስርኣተ አልበኝነት፣ ዝርፊያ፣ ሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ሙስናና ህገወጥ ንግድ እንቅስቃሴዎች በስፋት የሚታዩ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በቢሊየን የሚቆጠር እርዳታ ለጸጥታ አስከባሪው ክፍል ቢመደብም በወታደሩና በሲቪል ማህበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር ተዘውትሮ የሚገለጽ ቢሆንም ይህ ሁኔታ ቅኝ ግዛት ካለፈ ከአስር አመታት በህዋላም በስፋት የሚታይ ነው፡፡ ጠንካራ የሙያ ብቃት ያለው ወታደራዊ ሃይል የመገንባት አለመቻል ከሚያስከፍላቸው ዋጋዎች ውስጥ የማያቋርጥ አለመረጋጋት፣ የማይቆም ድህነት፣ መዋለ ንዋይ ፍሰትን ማገትን የዲሞክራሲ መኮላሸቶች ይጠቀሳሉ፡፡

ውጤታማና ተአማኒነት ያለው ወታደራዊ ሃይል በብዙ አፍሪካ ሃገሮች ለመገንባት ያለመቻሉ ምክኒያቶች ውስብስብ ናቸው፡፡ በአብዛኛው ግን ፖለቲካዊ ይዘት አላቸው፡፡ በቅኝ ግዛት ዘመን የአፍሪካ ወታደራዊ ሃይል የተመሰረተበት አላማ ለህዝብ ሳይሆን መንግስትን ከህዝብ ለመከላከል ነው፡፡ ለዚህም ማስተባበሪያ ብዙሃነትን ለመቆጣጠር ሲባል ከአናሳ ብሄሮች በአብላጫው ወደ ወታደራዊ ክፍሉ ይመለመሉ ነበር፡፡ ይህ አሰራር ከቅኝ ግዛት በሁዋላም ቀጥሎዋል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክኒያት ከአናሳው ብሄር የሚወጡ ወታደራዊ መሪዎች ለዲሞክሪያሲና የብዙሃን አመራር ፖለቲካዊ ለገምተኝነት ነው፡፡ በስርኣት ያልተዋቀረ ቁጥጥር እና ሚዛናዊነት የተጠላለፈ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ፍላጎቶች እየተጠናከሩ መጡ፤ በአንዳንድ ሁናቴዎች ቅኝ ግዛት ካለፈ አስርተ አመታት በሁዋላ ጎልተው ታይተዋል፡፡ በአፍሪካ ወታደራዊ ክፍሉን መቆጣጠርር ሃብትንና ስልጣንን መቆናጠጥ መሳሪያ ተደርጎ ተወስዶዋል፤ ሙስና ተሰራፍቶዋል፡፡ ይህም ወታደራዊ ክፍሉን፣ ፖለቲካዊ ይዘት እንዲኖረው ከማድረግ አልፎ፣ በወታደራዊ መሪዎችና በፖለቲከኞች መካከል የበላይነትን ለማግኘት የሚደረገውን ፉክክርና ግጭት አጠናክሮዋል፡፡ ይህ አካሄድ፣ ወታደራዊ ክፍሉን ብቃት ከማዳከም አልፎ፣ በህዝብ በኩል ጥርጣሬና ፍርሃትን ፈጥሮዋል፡፡ ይህም ለተጨማሪ አለመረጋጋትና አማጺያንን ለመዋጋት

ከህዝብ የሚገኘውን ድጋፍ ውስን እንዲሆን አድርጓል፡፡

ወታደራዊ የሙያ ብቃትን ለመገንባት እንቅፋት የሆኑትን ዘርፈ ብዙ ፈተናዎችን ለመስበር አቅም ግንባታ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ይልቁንም፣ መሰረታዊ የሆነውን ጸረ ለውጥ ዘገምተኛነት ለመለወጥና በሲቪል ማህበረሰቡና በወታደሩ መሃከል በጎአዊ ግንኙነት ለመመስረት ተከታታይነት ያለው እርምጃዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ተለምዶአዊ አካሄድ በቂ አይሆንም፤ የብሄራዊ ደህንነት ግምገማ ህዝቡን ያማከለ፣ የአፍሪካን ወታደራዊ ክፍል ስልጣንና ተግዳሮት የሚወስን፣ ብዙዎች የጸጥታ ችግሮች አገር በቀል ስለሆኑ ያስፈልጋል፡፡ የጸጥታ ሃይሉን መዋቅር በአዲስ መልክ ማደራጀት የሚነሱትን የጸጥታ ችግሮች በተሻለ ሁኔታ ለመለየት፣ ግዳጆችን በአንድ ወጥ መከላከያ ፖሊሲ ከማዋቀር አልፎ የወታደራዊ ክፍሉን አስፈላጊነት፣ የግዳጅ አፈጻጸም ብቃትን በህዝብ በኩል ያለውን ክብር ከፍ ያደርጋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሃገሪቱ መከላከያ ሃይል ለህዝብ ያለውን ሃላፊነት በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡ ስነ ምግባራዊ ህግጋቶች፣ ግብረ ገብነትን በመላው ሃይል ውስጥ እንዲሰርጽ ከማድረግ ስራ ጋር ታግዞ፣ ህገ መንግስታዊነት የተሙዋላ ስብእና፣ የማገልገል ስሜትና ሰብአዊ መብት ማክበርን ማስረጽ ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማስፈጸም ወታደራዊ ቅሬታ ሰሚ ክፍል፣ ከእዝ ሰንሰለት ውጪ፣ ወታደራዊ ህገጋትና ደንብ ጥሰቶችን የሚቆጣጠር ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ በተጓዳኝ ወታደራዊ ክፍሉን የፖለቲካ ይዘት እንዲኖረው የሚያደርጉ የፖለቲካና ወታደራዊ አመራሮች ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ መውሰድ ግድ ይላል፡፡ በአጠቃላይ፣ ወታደራዊ የሙያ ብቃትን ለማጎልበት የፖለቲካና የወታደራዊ መሪዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

በትክክለኛ መንገድ የብሄራዊ ደህንነት ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ወታደራዊ በጀት መዋሉን የሚያረጋግጥ ሁለገብ የሆነ የውስጥና የውጪ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች አስፈላጊ ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ፣ የጸጥታው ክፍል ላይ፣ ጊዜ ግብ ላይ ያተኮረ ቁጥጥር በህግ አውጪው ክፍል መደረግ ይኖርበታል፡፡ የአፍሪካ ህግ አርቃቂዎች ስለ ወታደራዊ ክፍሉ ግዴታ፣ የወደፊት ጉዞ፣ መርሆዎች፣ በጀት፣ የስልጣን እርከን አሰጣጥና የስራ አፈጻጸም በንቃት ማብላላትና መከራከር ይኖርባቸዋል፡፡ ስለ ወታደራዊ ክፍሉ መጫወት ስላለበት ሚናና የለውጥ ተቀባይነት መንግስት ነክ ያልሆኑ በተለይም የሲቪል ማህበረሰብ ሚዲያ ህብረተሰቡን በማንቃትና የቁጥጥሩ ክፍል እንዲሆን ማድረግ ይችላሉ፡፡

የወታደራዊ ሙያ ብቃት ከአፍሪካዊ እሴቶች ጋር ተዛማጅ ነው። ይሄም በተወሰኑ አፍሪካ አገሮች የታየ ነው። በፖለቲካውና በጸጥታ ሃይሉ መካከል ያለው ግንኙነት ሲቆረጥ ወታደሩ ክፍል ተከብሮና እንደ ህዝብ አዳኝ ተደርጎ ተቆጥሮዋል። ይህ አይነቱ አካሄድ በመላው አፍሪካ እንዲሰፍን የሁሉም አፍሪካዊ ህልምና ፍላጎት ነው። የአለመረጋጋትን፣ ድህነትን፣ የመልካም አስተዳደር ብልሹነትን መጥፋት በዚህ ላይ የተመሰረተ ነው።

## የአፍሪካ ወታደራዊ ክፍሎች ፈተናዎች

የ2012 የማሊ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት አገሪትዋንና የምእራብ አፍሪካን ክልል ወደ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ችግር ውስጥ ጨምሮዋል። ጥቂት የመስመር መኮንኖችና የበታች ሹም ወታደሮች የማሊን በህዝብ የተመረጠ መሪ አውርደው የ 21 አመት የዲሞክራሲን ተሞክሮና ሙያዊ ብቃት ያለው ወታደራዊ ክፍል ግንባታ ጥረት ከመንገድ አስወጡ። ከህገ መንግስታዊ ቀውሱ በተጨማሪ የማሊን የግዛት ደህንነት አደጋ ላይ ወደቀ፤ ለአክራሪ እስላሞች አመቺ የሆነ መንገድ በመፍጠር ሁኔታውን ለማረጋጋት የምእራብ አፍሪካ አገሮችና የፈረንሳይ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት አስፈልጓል። የምጣኔ ሃብትንና የግል መዋለ ንዋይ ፍሰትን በተመለከተ የደረሰው ኪሳራ አሻራ ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ነው።

እንደ አለመታደል፣ የወታደራዊ ሙያ ክህሎት አለመኖር በተደጋጋሚ የሚነሳ የአህጉሩ መታወቂያ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ወታደሩ በቀጥታ የዲሞክራሲ አካሄዱን ጣልቃ ገብቶ ያቋርጣል። ለምሳሌ፣ ከነጻነት መመለስ ጀምሮ፣ በቀድሞዋ የፖርቹጋል ቅኝ የነበረችው ጊኒ ቢሳው፣ አንድም በህዝብ የተመረጠ መሪ የምርጫ ዘመኑን በቢሮው የጨረሰ የለም። የጊኒ ቢሳው ህዝባዊ አብዮታዊ ጦር ሃይሎች፣ በሙስናና ህገወጥ እጽ ንግድ ላይ[1] በመሰማራቱ የሚታወቀው የወታደራዊ መሪዎችን ፍላጎት የሚጻረር መንግስት በማውረድ ታሪክ ያለው ነው። የ 2012 መፈንቅለ መንግስት የሁለተኛ ዙር ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ዋዜማ መፈንቅለ መንግስት የሚጠቀስ ነው። በግልጽ እንደሚታየው፣ የማሊም ሆነ የጊኒ ቢሳው ወታደራዊ ክፍል፣ በህዝብ የተመረጡ መሪዎችን ከስልጣን አግደዋል።

በሌላ ጊዜ፣ ደካማ ወታደራዊ የሙያ ክህሎት በተደጋጋሚ በሚነሱ ስርኣተ አልበኝነት ይገለጻል። ባለፈው አስርተ አመታት በአፍሪካ አህጉር

የተከሰተው ትልቁና አደገኛው ስርኣተ አልበኝነት የተከሰተው በቡርኪና ፋሶ ነው። በበታች ሹም መኮንኖችና ወታደሮች የተጀመረ ብጥብጥ እስከ 2011 አጋማሽ ድረስ ቀጥሎ ነበር። የዚህ ውጤት የሆኑት ዝርፊያ፣ አስገድ መድፈር፣ እንዲሁም የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በህዝቡ ውስጥ ታይቶ የማያውቅ ፍርሃትና የደህንነት ማጣት ስሜት ፈጥሮ ነበር። ማዳጋስካር በብዙ ወታደራዊ ስርኣተ አልበኝነት ተቀውጣለች። የዋና ከተማዋ አንታና ናሪቮ የቀድሞ ከንቲባ የነበረው አንድሪ ራጆሊና፣ በ 2009 በወታደሩ እርዳታ በህዝብ ከተመረጠ መሪ ስልጣኑን በመንጠቁ የተነሳ ምክኒያት ይህ ሆኖዋል። በዲሞክራቲክ ኮንጎ፣ በወታደራዊ ስርኣተ አልበኝነት እና ክህደት የተነሳ በመልሶ ማቋቋም፣ ትጥቅ ማስፈታት አካሄድ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ፈጥሮዋል።

ሌሎችም የወታደራዊ ሙያ ክህሎት መሸርሸሮች በአፍሪካ ይታይሉ። የናይጄሪያ ወታደር፣ ከአክራሪ እስላማዊ ከሆነው ከቦኮ ሃራም ጋር በሚያደርገው ጦርነት በርካታ የሰብአዊ መብት ጥሰት ፈጽምዋል የሚል ክስ ይቀርብበታል። ይህም የሚያሳየው ደካማ የእዝና የቁጥጥር ክህሎት ነው።[2] በተጨማሪም የሰሜኑን ናይጄሪያ ክፍል የማረጋጋቱን ተልእኮ አደናቅፎዋል። የዩጋንዳ መከላከያ ሰራዊት ላይ የሚነሳው ክስ፣ የዱር አራዊት ንግድ ተባባሪ በመሆን፣ ሌላው ሙስናን በተመለከተ ያለውን የስነ ምግባር ጉድለት አመላካች ነው።[3] የኬኒያ መከላከያ ሃይል ላይ ያነጣጠረው ክስ፣ የወስት ጌት ሞል በአልሸባብ በ 2013 ጥቃት ሲደርስበትና ከ 60 በላይ ሰዎች ሲሞቱ፣ ወታደሩ በዘረፋ ላይ መሰማራቱ የአፍሪካ ወታደራዊ ሙያ ክህሎት የት ደረጃ ላይ እንዳለ ለማሰብና ለመመርመር ተጨማሪ ምክኒያት ይሰጣል።[4]

በእርግጠኝነት፣ የተወሰኑ የአፍሪካ ሀገሮች የወታደራቸውን ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያስመሰግን ጥረት አድርገዋል። ነገር ግን፣ ከግማሽ ምእተ አመት ብዙዎቹ ሃገሮች ነጻነታቸውን ካገኙ በሁዋላ የአፍሪካ ማህበረሰቦች እንዴት አድርገው ሙያዊ ክህሎት ያለው የጦር ሃይል እንደሚመሰርቱ እንደገና ማየት አለባቸው። የደህንነት ፈተናዎቻቸውን ለመጋፈጥ ብቻ ሳይሆን፣ ጨቅላ የሆነውን ዲሞክራሲ ተሞክሮ ለማጠናከርና እድገትን ለማፋጠንም ይጠቅማል። የወደፊት ህልምንና እውነታውን በማገናዘብ፣ ይህ ጽሁፍ የአፍሪካን ወታደራዊ ሙያዊ ክህሎት ለማሻሻል የሚያጋጥሙትን ችግሮች ይመረምራል።

# የወታደራዊ ሙያ ክህሎት መመሪያዎች

ወታደራዊ ሙያ ክህሎት መሰረት የሚያደርጋቸው ወታደራዊ መዋቅሩ በዲሞክራሲያዊ ሲቪል እዝ ስር መሆን፣ መንግስታዊ ወገናዊነትና ሲቪል እዝ ስር መሆን፣ መንግስታዊ ወገናዊነትና ኢፖለቲካዊ መሆን፣ እንዲሁም ግብረ ገባዊ መዋቅራዊ ባህል ናቸው። እነዚህ መመሪያዎች አንድን ወታደራዊ የሙያ ክህሎት የተላበሰ ወታደር በሚያንጸባርቃቸው ስነ ስርኣት፣ ባህሪያዊ ልእልና፣ ክብር፣ ለግዳጅ ተገዢ መሆን፣ መስዋእትነት ይገለጻሉ። እነዚህ እሴቶች እንዲዳብሩ በግልጽ የተቀመጠ የእዝ ሰንሰለት፣ አላማ፣ ተጠያቂነትና የስራ አፈጻጸም ደንብ አስፈላጊ ናቸው። ምንም እንኳን የማያኮራ ታሪክ በዚህ ረገድ ቢታይም፣ እነዚህ የሙያዊ ክህሎት መመሪያዎች በአፍሪካ ወታደራዊ መሪዎችና በተራው ህዝብ ተአማኒነት አላቸው። ችግሩ ያለው፣ በብዙ የአፍሪካ አገሮች ወደ ተግባር ለመቀየር የተደረገው ጥረት መደናቀፍ ነው።

## ዲሞክራሲያዊ ሉኣላዊ ስልጣን

ለወታደራዊ ሙያ ክህሎት መሰረቱ የዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ባህል ነው። ሳሙኤል ኢ ፋይነር በመጽሃፉ ዘ ማን ኦን ሆርስባክ፡ የወታደሩ ሚና በፖለቲካ እንደገለጸው የአንድ አገር ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ባህል የሚመዘነው በአብዛኛው ህዝብ ስለፓለቲካ ስልጣን ሽግግሩ ሂደት ያለው አመኔታና የመጨረሻው ሉኣላዊ ስልጣን ባለቤት ዜጎች የመሆናቸው ግንዛቤ ነው።[5] በተጨማሪም የዲሞክራሲያዊ ሂደት በመንግስት ተቋሞች እንደ ጦር ሃይሉ የመሳሰሉት መደገፍ እና መጠበቅ አለበት። ወታደራዊ የሙያ ክህሎትን በተመለከተ መካተት ያለባቸው ገዢ ሃሳቦች፤ ዲሞክራሲያዊ ተቋሞችን ህጋዊ ልእልና መቀበል፣ በፖለቲካ ሂደት ውስጥ ወገናዊ አለመሆን፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር እውቅና መስጠት ናቸው። ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ባህል ሲኖር የፖለቲካና ህዝብን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሙሉ ሃላፊነት የሚወድቀው በህጋዊ መንገድ የተመረጠው የሲቪል ስልጣን ላይ ነው። የመከላከያ ሃይሉ ሃላፊነት የሚወሰነው በሲቪል አስተዳደሩ የሚነደፉ የጸጥታና የመከላከያ ፖሊሲዎችን ማስፈጸም ላይ ነው።

አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሃገሮች እነዚህን የዲሞክራሲያሲ እሴቶችና፣ መሰረታዊ የወታደራዊ ሙያ ክህሎት መመሪያዎች በህገ መንግስታቸውና

በወታደራዊ ፍልስፍና መርሆዎቻቸው አስፍረዋቸዋል፡፡ ወደ ዲሞክራሲ በመሸጋገር ላይ ያሉ በርካታ የአፍሪካ ሃገሮችም ይጋሩዋቸዋል፡፡ ከዚህም አልፎ፣ በርካታ ወታደራዊ መሪዎች በምእራቡ ኣለም ኮሌጆች ስልጠናቸው ከነዚህ እሴቶች ጋር ተዋውቀዋል፡፡ ማስተዋል የሚገባን፣ እነዚህ እሴቶች በአፍሪካ ባህል ውስጥ ስር የሰደደ ነባራዊነት እንዳላቸው ነው፡፡ ህብረተሰቡን በተመለከተ፣ ግዛትን መከላከል፣ ለንጉስ መገዛት፣ ታማኝነት፣ ልእልና፣ የአፍሪካ ቀደምት ተፋላሚዎች ዋኖቹ መሪዎች ነበሩ፡፡ በሲቪልና በወታደር መካከል ያለው ግንኙነት የተፈረካከሰው በቅኝ ግዛትና ድህረ ቅኝ ግዛት በሁዋላ ነው፡፡ አዲስ የተፈጠሩት የአፍሪካ ሃገሮች ነጻ መንግስት መሆናቸውን ለማሳየት ነው ጦር የመሰረቱት፡፡ በአንጻሩ የተመሰረተው ጦር ሃይል ተልኮ ገዢውን ክፍል ደህንነት መጠበቅ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እያየነው ያለነው፣ ታሪካዊ የሆነውን የወታደራዊ ሙያ ክህሎት መሰረታዊ የሆኑትን እሴቶች ለማስመለስ የሚደረግ ትግል ነው፡፡

## ወገናዊነት

ብቃት ያለው ጦር ለመመስረት ግልጽና ሚዛናዊ የሆነ ወገናዊነት ለመንግስትና ለሲቪል ማህበረሰብ የሚሰጥ አክብሮት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ በሲቪል ማህበረሰብና በመንግስት መካከል ለሚነሱ የተጡዋጡዋፉ ውይይትና ክርክሮች መሃል ጣልቃ አለመግባትንም ይጨምራል፡፡ የዲሞክራሲ ጉዞ ዋዣቂና ያልተረጋጋ ነው፡፡ ጊዜያዊ አለመረጋጋትን በሚፈጥሩ ተዋናዮች መንገዱን እንዲስት ሊደረግ ይችላል፡፡ ያለ ወታደሩ ጽኑ የሆነ አቋም ለኢወገናዊነት እና ለዲሞክራሲያዊ ልእልና ላለው ስልጣን ድጋፍ ለመስጠት፣ የዲሞክራሲያዊ ሂደቱ እራሱን በራሱ እያስተካከለና እየተጠናከረ ለመሄድ ይቸገራል፡፡[6]

አንድ የአፍሪካ ወታደራዊ ተቋም በነዚህ መመሪያዎች የሚመራ የሴኔጋል የጦር ሃይል ነው፡፡ ከነጻነት በሁዋላ ሴኔጋል የመፈንቅለ መንግስት አልታየባትም፡፡ የሴኔጋል ዲሞክራሲ ባህል በየጊዜው ፈተናዎች ቢያጋጥሙትም ወታደራዊ ክፍሉ ህገ መንግስታዊ ስርኣቱን የሚፈታተን አካሄድ አላሳየም፡፡ እነዚህን ፈተናዎች በመቋቋም፣ የሴኔጋል ዲሞክራሲያዊ ባህል ባለፉት አመታት እየተጠናከረ መጥቶዋል፡፡

ከሴኔጋል በተጨማሪ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ያላስተናገዱ ጥቂት የአፍሪካ ሃገሮች ውስጥ ቦስትዋና፣ ኬፕ ቨርዲ፣ ሞዛምቢክ፣

ናሚቢያ እና ዛምቢያ ይገኛሉ።[7]

ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ያስተናገዱ ሃገሮች ጦራቸው ለፈጸመው ያልተገባ ጣልቃ ገብነት ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል። አንዱ የመፈንቅለ መንግስት ታሪካዊ ማገናዘቢያነት እውን ከሆነ፣ ተከታታይ መፈንቅለ መንግስት ተግባራዊ የመሆን እድል ይጨምራል። እውነታው፣ 65 ከመቶ ከሰሃራ በታች አገሮች መፈንቅለ መንግስት አስተናግደዋል። 42 ከመቶ የሚሆኑት ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግስት አይተዋል።[8] አብዛኛዎቹ የአፍሪካ የመፈንቅለ መንግስቶች ያነጣጠሩት እራሱ በመፈንቅለ መንግስት ስልጣን በያዘ መንግስት ላይ ነው። ከ 1960 እስከ 2012 ድረስ፣ ዘጠኙ በሱዳን የተደረጉት የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ያነጣጠሩት ወታደራዊ አገዛዝ ላይ ነው። በ ጋና ከተደረጉት ዘጠኙ፣ ሰባቱ የተደረጉት በተመሳሳይ ሁናቴ ነው። አንዴ ከተከሰቱ፣ እነዚህ ቅድመ ሁናቴዎች ለማስወገድ የሚያስቸግሩ ሸክም ከመሆናቸውም በላይ ለአንዳንድ መንግስታት ስርኣት መዋዥቅና ብሎም መውደቅ ምክኒያት ሆነዋል። የመሻሻል ሂደቱን ለማነጻጸር፣ ምንም እንኳን አሁንም የመፈንቅለ መንግስት አደጋ በአፍሪካ የሚያስፈራ እውነታ ቢሆንም፣ የአፈጻጸም ፍጥነቱ ግምት ውስጥ በሚገባ መልኩ ቀንሰዋል። ከ2000 አጋማሽ ጀምሮ (በአብዛኛው የሚፈጸመው በምእራብ እና በመካከለኛው አፍሪካ ነው) (ሰንጠረዥ 1 ይመልከቱ)

### ሰንጠረዥ 1. የአፍሪካ አገሮች የመንግስት ግልበጣ ቁጥር እና አይነት 1960-2012

| አመት | የተሳካ | የከሸፈ/ ሙከራ |
|---|---|---|
| 1960 | 1 (ዲአርሲ) | 1 (ኢትዮጵያ) |
| 1961 | | 1 (ሶማሊያ) |
| 1962 | | 1 (ሴኔጋል) |
| 1963 | 3 (ቶጎ,ኮንጎ,ቤኒን) | 1(ዲአርሲ) |
| 1964 | | 4 (ጋና, ታንዛኒያ , ጋቦን, ዲአርሲ) |
| 1965 | 5 (ቤኒን,አልጄሪያ, ዲአርሲ, ቤኒን, ቤኒን) | 1 (ቡሩንዲ) |
| 1966 | 8 (ሲኤአር, ናይጄሪያ, ዩጋንዳ, ጋና, ቡርኪና ፋሶ, ቡሩንዲ, ናይጄሪያ, ቡሩንዲ) | 2 (ቶጎ, ሱዳን) |
| 1967 | 3 (ቶጎ, ሴራ ሊዮን, ቤኒን) | 1 (ጋና) |
| 1968 | 3 (ሴራ ሊዮን, ኮንጎ, ማሊ) | |
| 1969 | 4 (ሊብያ, ሱዳን, ሶማሊያ, ቤኒን) | |

| አመት | የተሳካ | የከሸፈ/ ሙከራ |
|---|---|---|
| 1970 | | 3 (ኮንጎ, ቶጎ, ጊኒ) |
| 1971 | 1 (ዩጋንዳ) | 4 (ሴራ ሊዮን, ዩጋንዳ, ሱዳን, ቻድ) |
| 1972 | 2 (ጋና, ማዳጋስካር, ቤኒን) | 2 (ኮንጎ, ቤኒን) |
| 1973 | 2 (ስዋዚላንድ, ሩዋንዳ) | 1 ((ኮት ዲቭዋር) |
| 1974 | 3 (ቡርኪና ፋሶ, ናይጄሪያ, ኢትዮጵያ) | 5 (ዩጋንዳ, ዩጋንዳ, አንጎላ, ሲኤአር, ማዳጋስካር) |
| 1975 | 2 (ቻድ, ናይጄሪያ) | 3 (ቤኒን, ሱዳን, ሞዛምቢክ) |
| 1976 | 1 (ቡሩንዲ) | 6 (ሲኤአር, ናይጄሪያ, ኒጀር, ዩጋንዳ, ማሊ, ሱዳን) |
| 1977 | 1 (ሲሼልስ) | 6 (ቤኒን, ሱዳን, ኮንጎ, ቻድ, አንጎላ, ዩጋንዳ) |
| 1978 | 3 (ኮሞሮስ, ጋና, ሞሪታኒያ) | 3 (ማሊ, ሶማሊያ, ሱዳን) |
| 1979 | 3 (ጋና, ኢኳቶሪያል ጊኒ, ሲኤአር) | 2 (ቻድ, ጋና) |
| 1980 | 5 (ሞሪታኒያ, ላይቤሪያ, ዩጋንዳ, ጊኒ-ቢሳው, ቡርኪና ፋሶ) | 1 (ዛምቢያ) |
| 1981 | 2 (ሲኤአር, ጋና) | 4 (ሞሪታኒያ, ኢኳቶሪያል ጊኒ, ላይቤሪያ, ጋና) |
| 1982 | 1 (ቡርኪና ፋሶ) | 5 (ሞሪታኒያ, ሲኤአር, ዚምባቤ, ኬኒያ, ጋና) |
| 1983 | 2 (ቡርኪና ፋሶ, ናይጄሪያ) | 5 (ኢኳቶሪያል ጊኒ, ላይቤሪያ, ጋና, ካሜሩን, ኒጀር) |
| 1984 | 2 (ጊኒ, ሞሪታኒያ) | 2 (ጋና, ካሜሩን) |
| 1985 | 3 (ሱዳን, ዩጋንዳ, ናይጄሪያ) | 3 (ላይቤሪያ, ጊኒ, ላይቤሪያ) |
| 1986 | 1 (ሌሶቶ) | 1 (ኢኳቶሪያል ጊኒ) |
| 1987 | 2 (ቡሩንዲ, ቡርኪና ፋሶ) | 2 (ሴራ ሊዮን, ኮሞሮስ) |
| 1988 | | 1 (ዩጋንዳ) |
| 1989 | 2 (ሱዳን, ኮሞሮስ) | 1 (ኢትዮጵያ) |
| 1990 | 1 (ቻድ) | 2 (ናይጄሪያ, ዛምቢያ) |
| 1991 | 2 (ማሊ, ሌሶቶ) | 4 (ጅቡቲ, ቶጎ, ቻድ, ቶጎ) |
| 1992 | 2 (ሴራ ሊዮን, አልጄሪያ) | 3 (ቡሩንዲ, ቤኒን, ኮሞሮስ) |

| አመት | የተሳካ | የከሸፈ/ ሙከራ |
|---|---|---|
| 1993 | 1 (ናይጄሪያ) | 2 (ጊኒ-ቢሳው, ቡሩንዲ) |
| 1994 | 1 (ጋምቢያ) | 2 (ቡሩንዲ, ላይቤሪያ) |
| 1995 | | 3 (ሳኦ ቶሜና ፕሪንሲፔ, ኮሞሮስ, ሴራ ሊዮን) |
| 1996 | 3 (ሴራ ሊዮን, ኒጀር, ቡሩንዲ) | 3 (ጊኒ, ሲኤአር, ሴራ ሊዮን) |
| 1997 | 1 (ሴራ ሊዮን) | 1 (ዛምቢያ) |
| 1998 | | 1 (ጊኒ-ቢሳው) |
| 1999 | 3 (ኒጀር, ኮሞሮስ, ኮት ዲቭዋር) | |
| 2000 | | 3 (ኮሞሮስ, ሴራ ሊዮን, ኮት ዲቭዋር) |
| 2001 | 1 (ዲአርሲ) | 5 (ኮት ዲቭዋር, ቡሩንዲ, ሲኤአር, ቡሩንዲ, ኮሞሮስ) |
| 2002 | 1 (ኮት ዲቭዋር) | |
| 2003 | 3 (ሲኤአር, ሳኦ ቶሜና ፕሪንሲፔ, ጊኒ-ቢሳው) | 1 (ሞሪታኒያ) |
| 2004 | | 4 (ዲአርሲ, ቻድ, ዲአርሲ, ኢኳቶሪያል ጊኒ) |
| 2005 | 1 (ሞሪታኒያ) | |
| 2006 | 1 (ቻድ) | 2 (ማዳጋስካር, ኮት ዲቭዋር) |
| 2007 | | |
| 2008 | 2 (ሞሪታኒያ, ጊኒ) | |
| 2009 | | 1 (ማዳጋስካር) |
| 2010 | 1 (ኒጀር) | 2 (ማዳጋስካር, ጊኒ-ቢሳው) |
| 2011 | | 3 (ዲአርሲ, ኒጀር, ጊኒ-ቢሳው) |
| 2012 | 2 (ማሊ, ጊኒ-ቢሳው) | |

ምንጭ፡ ባርካ እና ንኩቤ፣ ሴፕቴምበር 2012.[9]

ተጠቃሽ ምክኒያቶቹ፣ እንደ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ድክመት፣ ሙስና፣ ተቋማዊ የዲሞክራሲ አደረጃጀት አለመኖር፣ ለጦር ሃይሉ በሃይል የመንግስት ስልጣን ለመጎልበት በር ከፋቾች ናቸው። በማያስገርም መልኩ፣ ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያላቸው ከሰሃራ በታች ያሉ ሃገሮች ከፍተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ

ካላቸው ሃገሮች በበለጠ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት አስተናግደዋል፡፡[10] ሆኖም፣ ከጥቂቶቹ በስተቀር፣ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት መሪዎቹ፣ መረጋጋት ማምጣትም ሆነ ስልጣን ለሲቪሉ ክፍል መመለስ ሳይሳናቸው ቀርቶዋል፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ፣ ወታደር መራሽ አገዛዝ ለሃገር ኢኮኖሚ አፍራሽ ተጽእኖ ሲኖረው በዚህም የጥፋቱ አዙሪት እድሜ የተራዘመ ይሆናል፡፡ ጊኒ፣ ማሊ፣ ሞሪታኒያ፣ ናይጄሪያ፣ ከመፈንቅለ መንግስት ክስተት በሁዋላ ኣመታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው በ 4.5 ከመቶ ወርዶዋል፡፡[11] ምስል 1 እንደሚያሳየው ተደጋጋሚ የመፈንቅለ መንግስትና የአገሮች የረዥም ጊዜ የኢኮኖሚ እድገት ያላቸውን ተጻራሪ ዝምድና ያሳያል፡፡ ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግስት ጥቂት የአፍሪካን ሃገሮች እንደ ቡሩንዲ፣ ኮሞሮስ፣ ሴንትራል አፍሪካ ሪፑብሊክ፣ ኮንጎና፣ ጊኒ ቢሳዎ፣ የመሳሰሉትን ለኢኮኖሚያዊ ዝቅጠት ዳርጓቸዋል፡፡ በዚህ ውስጥ የማትካተት፣ እንደ ኢኩዋቶሪያል ጊኒ በተፈጥሮ ሃብትዋ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ እድገት ቢታይባትም እድገቱ የህዝቡን ኑሮ ከማሻሻል ጋር የተገናዘበ አይደለም፡፡ አለመረጋጋት መዋለ ንዋይ ፍሰትንና እድገትን ያደናቅፋል፡፡ በተፈጥሮ ሃብት ላይ ያልተመሰረቱ ኢኮኖሚ ያላቸውና፣ ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ያሳዩ ሃገሮች፣ ተመሳሳይ በሚባል መልኩ መፈንቅለ መንግስት ያላስተናገዱ ወይም ጥቂት ብቻ ያስተናገዱ ሃገሮች ናቸው፡፡

ሳሙኤል ሃንቲንግተን እንደሚለው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት በመንግስት ጉዳይ፣ ወታደራዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ ችግር ነው፡፡ የአፍሪካ አገሮች በተመለከተ ይህ እይታ ከሁኔታዎች ጋር ተዛማጅነት አለው፡፡[12] መሰረት የጣለ ህግና ደንብ፣ ጠንካራ የዴሞክራሲ ተቋማት በሌሉበት ሁኔት፣ የፖለቲካ ሂደቱን ለመቆጣጠር፣ የሰራተኛ ማህበራት፣ ተማሪዎች፣ የሃይማኖት ሰዎች፣ ተጽእኖ ፈጣሪዎችና ወታደሩ በሙሉ የመንግስት ስልጣን ለመቆጣጠር ወደ ፖለቲካ ውድድር ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ከድህረ ቅኝ ግዛት በሁዋላ ስላለው የአፍሪካ ሁኔታ መገለጫ ነው፡፡ ተጽእኖ ፈጣሪነታቸውንና አንጻራዊ ግዝፈታቸውን ስናገናዝብ የአፍሪካ ወታደራዊ ክፍል፣ በፖለቲካው አለም ትልቁን ሚና ተጫዋች ሆነዋል፡፡ ይህንንም ተመራጭ ያደረጋቸውን ሁኔታ ተጠቅመውበታል፡፡

**ምስል 1. ጂዲፒ በነፍስ ወከፍ እድገት እና የመፈንቅለ መንግስት ብዛቶች (የተሳኩ እና የተሞከሩ) በተመረጡ ከሰሃራ በታች አገሮች፣ 1960-2012**




ምንጭ፡ ባርካ እና ንኩቤ፣ ሴፕቴምበር 2012.[13]

የጋራ የሆኑ የሀብት ፍላጎቶች ያገናኛቸው ከፍተኛ ወታደራዊ ባለስልጣናት፣ ፖለቲከኞች፣ የኢኮኖሚ ዘርፉ መሪዎች እንዲሁም የውጪ ሃገር ሸርከኞች መፈጠር፣ የወታደሩን ጣልቃ ገብነት ውስብስብና በቀላሉ ለመለየት የሚያስቸግር አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ፣ በአንጎላ፣ ወታደሩ ክፍል አባላት ከውጪ ካምፓኒዎች ጋር በሚደረግ የኮንትራት ስምምነት ላይ ይሳተፋል፡፡[14] የኮርፖሬት ቦርድ አባል ይሆናሉ፤ የቴሌኮም ካምፓኒዎች አብላጫውን ድርሻ ባለቤት ናቸው፡፡ በተለያዩ ጊዜ ናይጄሪያን ያስተዳደሩ ወታደራዊ መንግስታት በኢኮኖሚው መልክ ትልቅ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ወታደራዊ መኮንኖችን የካምፓኒ ቦርድ ዳይሬክተርና ከፍተኛ የፖለቲካ ቢሮዎችን እንዲይዝ ማድረግ፤ ከፍተኛ ሀብት እንዲያጋብሱና የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት እንዲሆኑ ረድቶዋቸዋል፡፡ ብዙዎቹ በጡረታ ከተገለለ በሁዋላም ቢሆን በናይጄሪያ ፖለቲካ ዋና ተዋናይ ሆነው ቀጥለዋል፡፡

በ 1999 የናይጄሪያ ህዝብ የ ኦሊሴንጎ ኦባሳንጆን ዲሞክራሲያዊ መንግስት ሲመርጥ ለ 16 አመታት በስልጣን ላይ የቆየው ወታደራዊ አገዛዝ ፍጻሜ ሆነ፡፡ አዲሱ መንግስት የረዥም ዘመን የወታደሩ በንግዱ ዘርፍ ጣልቃ መግባት በተአማኒነቱ እና በስራ አፈጻጸሙ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ በሚገባ ተረድቶ ነበር፡፡ በፍጥነትም በርካታ መኮንኖችን በጡረታ አሰናብቶ፣ የነዳጅ ፈቃድ ሰርዞ፣ ለከፍተኛ መኮንኖች ተሰጥቶዋል ተብለው የተጠረጠሩ መሬቶችን ወረሰ፡፡[15] ይህ የጻጥታውን ዘርፍ ለማሻሻል የሚደረገው የናይጄሪያ ጥረት በቀጣይነት እየተካሄደ ነው፡፡

መከላከያውን ለግል ብልጽግና መጠቀም በህዝብ በኩል ያለውን የማገልገል ፍላጎት በማዳከሙ ክህደት ያለው ጦር ለመመስረት አዳጋች ይሆናል፡፡ በተዛማጅ የጦሩን የስራ ፍላጎትና ሀገሩንና ህዝቡን ለመከላከል ያለውን ፍላጎት ያዳክማል፡፡ ከ 2,400 አመት በፊት ፕሌቶ እንዳመላከተው የወታደሮች በሌላ የሙያ ዘርፎች ጣልቃ መግባት ሃገር ይጠፋል፡፡"[16]

## በግብጽ የተወሳሰበው የወታደርና ሲቪሉ ማህበረሰብ ግንኙነት

"ሁለተኛው የግብጽ ሪፐብሊክ ወደ ህይወት ያመጣው፣ ወታደራዊው ሪፐብሊክ ከጠፋ በሁዋላ ነው፡፡[17] ይህ አስፈሪና ድባብ የተላበሰ ማስጠንቀቂያ የሚያመላክተው አስርተ ኣመታት ያስቆጠረውን የግብጽ የሲቪልና የወታደሩን የተወሳሰበ ግንኙነት ነው፡፡ በ 1952 ንጉስ ፋሩቅን

ከመንበራቸው ካስወገደች በሁዋላ በወታደራዊ ፍንቀላ፣ ግብጽ የይስሙላ ሪፐብሊክ ሆነች። የመጀመሪያው ፕሬዚደንት፣ ጋማል አብደል ናስር፣ ወታደራዊ መኮንን የነበሩ ናቸው። ሌሎችም ከሳቸው በሁዋላ የመጡት አንዋር ሳዳት፣ ሆስኒ ሙባረክ፣ ወታደራዊ መኮንኖች ናቸው። 59 አመት ወታደራዊ አገዛዝ ይሸፍናል። ከማንኛውም ፖሊስ ውሳኔ ጀርባ ያለው ሃይል ወታደሩ ነው። የመንግስት ሃብት የነበሩ ተቋሞች በወታደሩ ስር ወደቁ።[18] በርካታ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፣ ከልጆች መዋያ ማዕከል እስከ የባህር ዳር መዝናኛ ሆቴሎችና ጋዝ ማደያዎች ጭምር በወታደሩ ይዞታ ስር ወደቁ። እንዲህም ሆኖ ማንኛውንም አይነት ገቢ ለመንግስት አያሳውቅም።[19]

የ 2011 አረብ ስፕሪንግ፣ ይህንን ተለምዶአዊ አሰራር የሚሰብሩ ሁናቴዎች እንዲፈጠሩ አደረገ። ቁጥሩ ብዙ የሆነው የህዝብ አመጽ የወታደሩን ክፍል የሀገር ህልውና አደጋ ላይ ሊወድቅ ነው ብሎ እንዲያስብ አደረገው። በዚህም የሆስኒ ሙባረክን ከስልጣን መወገድና መታሰር አቀነባበረ። የወታደሩ ክፍል፣ በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የሃይል እርምጃ ባለመውሰዱ ከሀገር ውስጥና ከውጪ አድናቆት ተቸረው። ወዲያውኑ ወታደሩ በከፍተኛ የጦር ሃይሎች ምክር ቤት ጥላ ስር በመሆን የመንግስት ስልጣንን ተቆጣጠረ።

በተጋረጠበት የኢኮኖሚ ችግር ላይ የአገር ውስጥና የውጪ ተቃውሞ ስለበረታበት አዲስ ህገ መንግስት ለማርቀቅ የጥድፊያ ስራ ጀመረ። የፓርላማና ፕሬዝደንታዊ ምርጫ ጊዜ ወሰነ። በ 2011 መጨረሻ የፓርላማ ምርጫ ተካሄደ፤ በውጤቱም የሰላምና ፍትሕ ፓርቲ፣ የእስልምና ወንድማማች ፓርቲ በሚል በሚታወቀው አብላጫውን ወንበር በማግኘት በአሸናፊነት ወጣ።

የፕሬዝደንታዊ ምርጫ ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ሲቀረው በ 2012 ሰኔ ወር የወታደሩን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ለመከላከል በማሰብ፣ ከፍተኛው ወታደራዊ ምክር ቤት፣ ተጨማሪ ህገ መንግስታዊ አዋጅ አስተላለፈ። ወታደራዊ ምክር ቤት ሙሉ በሙሉ ወታደራዊ ጉዳዩን በተመለከተ ስልጣኑን በስሩ አደረገ። ህገ መንግስቱን ለማርቀቅ በተቋቋመው ኮሚቴ ውስጥ ከፍተኛውን ሚና ለመጫወት የሚያስችለውን ቦታ ወሰደ።

መሀመድ ሞርሲ የግብጽ የመጀመሪያው በምርጫ አሸንፈው ፕሬዝደንት ከሆኑ በሁዋላ ህገ መንግስታዊ ማሻሻያ አዋጅ ያወጁትን ጀነራሎች አባረሩ። ነገር ግን፤ የከፍተኛ ወታደራዊ ምክር ቤት ለራሱ ያዳላደለውን ስልጣን ለመቀልበስ ሳይቻላቸው ቀረ። ታደሮቹ አዲሶቹ የሲቪል አስተዳደር መሪዎች የአስተዳደር ጉዳይ ላይ ስምምነት ላይ የደረሱ መስለው ታዩ፤ ስጋት የተሞላበት ቢሆንም ወታደሩ ከአስተዳደር ጉዳዮች አፈገፈገ። አልፎ ተርፎም፣ የከፍተኛ ጄኔራሎቹን በፕሬዝደንት ሞርሲ መባረራቸውን አሜን ብሎ ተቀበለ።

በመቀጠልም፣ በታህሳስ 2012 በህዝብ ድምጽ የጸደቀው ህገ መንግስት የወታደሩን ክፍል ነጻ ራስ ገዝነት ህጋዊ እውቅና ሰጠው። በዚህም፣ የመከላከያ ሚኒስቴር ቦታ ለወታደራዊ መኮንን የተተወ ሆነ። ፓርላማ ወታደራዊ በጀትን አይቆጣጠርም። በጀቱን የሚቆጣጠር ስልጣን ያለው

ከፍተኛው ወታደራዊ ምክር ቤት ሆነ፡፡ ወታደራዊ ምክር ቤቱ 15-አባላቶች ሲኖሩት 8ቱ[20] ወታደሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም መንግስትና ህዝብ ስለወታደሩ ክፍል በጀት አጠቃቀም ምንም እውቀት እንዳይኖራቸው አደረገ፡፡ በዚህም የተነሳ፣ ወታደሩ ክፍል፣ ባለው ስልጣን በመጠቀም ተነግሮ የማያልቅ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ማጋበስ ቀጠለ፡፡ ከቴሌቪዥን እስከ የወይራ ዘይት ምርት የወታደሩ ሰፊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከቀረጥ ነጻ ናቸው፡፡ ወታደሮቹን እንደ የቀን ጉልበት ሰራተኛ ከማሰራት ጀምሮ በህዝብ ባለቤትነት ስር ያሉ መሬቶችን ለራሱ በሚመች ዋጋ መግዛትን ይጨምራል፡፡[21]

የፕሬዝደንት ሞርሲ አግላይ የሆነ አስተዳደር መንገድ፣ ሁሉን ነክና በግልጽ ያልታወቀ ስልጣን፣ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ቀውስ፣ እስላም አክራሪዎች በግብጽ ህዝብ ላይ የበላይነት እያገኙ ነው ከሚል ፍራቻ የመጣ መከፋፈል፤ በ 2012 ህገ መንግስት ህጋዊነት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች በግብጽ ማህበረሰብ ውስጥ ውጥረት ፈጠሩ፡፡ መጠነ ብዙ የሆነ ህዝባዊ ተቃውሞ ሰልፍ በሰኔ 2013 ለወታደሩ ክፍል ጣልቃ ለመግባት እድል ፈጠረ፡፡ በሀምሌ 2, የብሄራዊ ደህንነትን ለመጠበቅ በሚል ፕሬዝደንት ሞርሲ በወታደሩ ከስልጣን ተወገዱ፡፡ በተከታታይም ፕሬዝደንት ሞርሲን ለመደገፍ በወጡ ሰልፈኞች ላይ የሃይል እርምጃ ወሰደ፡፡ የሙስሊም ብራዘርሁድ መሪዎችን አሰረ፡፡ ይህ የሃይል እርምጃ ከ 1,000 በላይ የሰው ህይወት አጥፍቶዋል፡፡

በሚቀጥለው አመት፣ ለወታደሩ ክፍል አደጋ ናቸው የተባሉ ወደ 20,000 የሚገመቱ ሰዎች ታሰሩ፡፡ የሲቪል ማህበረሰቡና ነጻ ሚዲያ ላይ ማቀብ ተጣለ፡፡ አዲስ በጸደቀው የ 2014 ህገ መንግስት ወታደሩ ክፍል በጀቱን በተመለከተ ራስ ገዝ መሆኑን፣ ከወታደራዊ ፍርድ ቤት ውጪ አባላቶቹ ያለመጠየቅ መብት እንዳላቸው፣ ሲቪል የማህበረሰቡን ክፍል በወታደራዊ ፍርድ ቤት መዳኘት የሚያስችለው ህግ አጸደቀ፡፡[22] በተጨማሪም ስልጣኑን በማስፋት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ከቀን ለቀን ፍጆታ እቃዎች የጠርሙስ ውሃ፣ የቤት ፈቃዶች አንስቶ እስከ ትላልቅ የግንባታ ስራዎች፣ ሃይል ማመንጫና ቴክኖሎጂ ነክ ፕሮጀክቶቹ ውስጥ ገባ፡፡[23] ጎን ለጎንም፣ የወታደሩ ክፍል፣ ለበላይ አዛዡ ጄኔራል ፋታህ አል ሲሲ ሁኔታዎችን አመቻችቶ በ 2014 (ያለ ተቀናቃኝ 96 ከመቶ የሆነውን ድምጽ በማሸነፍ መንበረ ስልጣኑን እንዲይዝ አደረገ፡፡

ምንም እንኳን ወታደሩ በግብጽ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና ተጫዋችን በመመልከት ወደ ትክክለኛ ቦታዬ ተመልሼያለሁ ብሎ ቢያስብም በግልጽ እንደሚታየው የብቁ ወታደራዊ ሙያ ክህሎት መመሪያዎችን ተግባራዊ ሳያደርግ ቀርቶዋል፡፡ እነዚህም መመሪያዎች ለዲሞክራቲክ የሲቪል ስልጣን መገዛት፣ ለህግ ተገዢ መሆንና ለተቋሙ ግብረ ገባዊ መርሆዎች አክብሮት ናቸው፡፡ የግብጽ ሁኔታ እንደሚያሳየው ወታደራዊ ተቋሙ አንዱን የብቁ ወታደራዊ ክህለት መመሪያ ማክበር ካቃተው የተቀሩትን ለማክበር ይቸገራል፡፡

## ስነ ምግባራዊ ተቋም

ከዴሞክራቲክ የሲቪል ስልጣን በወታደሩ ላይና ወታደሩ ለመንግስት ያለው ወገናዊነት በተጨማሪ፣ ብቁ ወታደራዊ ክህሎት ያለው ሃይል ለመገንባት የስነ ምግባር ባህል በቅድመ ሁኔታ የሚቀርብ ነው፡፡ በዚህ እሴት ውስጥ የሚካተቱ፣ ችሎታን መሰረት ያደረገ እድገት፣ ወታደሮችና መሪዎቻቸው ለሚፈጽሙት ድርጊት ተጠያቂ መሆንና አድሎአዊነት የሌለበት ሰብአዊና ብቃት ያለው የጸጥታ ማስከበር ስራ ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት እሴቶቹ ተፈጥሮዊ ሁሌም ያሉ አይደሉም፡፡ በስልጠናና በትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡ ወታደሮቹ በተለየ የስነ ምግባር ስልጠና መታነጽ አለባቸው፡፡ ስነ ስርዓት፣ ህግ፣ ውጊያ ስልት እንደሚማሩት ሁሉ፣ ወታደራዊ ክፍሉ በትልቁ ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ባገናዘበ ሁኔታ ነው፡፡

በወታደራዊ ተቋም ባህል የወታደር መርሆ አስፈላጊው ምሰሶ ነው፡፡ ለተልእኮውም፣ መሳካት ከተገቢው ወታደራዊ ልምምድ በተጓዳኝ፣ ወታደሮች የሀገርን ጥቅም ከራሳቸው የማስቀደም ድፍረት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከክፍያም በላይ፣ ጀግንነት፣ ተገዢነት፣ መስዋእትነትና የሃገርን ህዝብ ከአደጋ መከላከልና መጠበቅ አጓጊና አነሳሽ ናቸው፡፡ ወታደሮች ለሙያዎች ፍቅር ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ ከፍተኛ ክህሎት ያለው ወታደር መሆን ማንም ሊሆነው የሚችለው አይደለም፡፡’

እነዚህ መመሪያ እሴቶች ከፍተኛ ክህሎት ያለው ሰራዊት ለመገንባትና ለማቆየት በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በቦተሱዋና፣ መከላከያ ሃይል አባላቶች ጭምር የቦተሱዋና መከላከያ ሃይል በሃገሪቱ ውስጥ ካሉ ስነ ምግባራዊ አገልግሎት ሰጪዎች መሃከል የላቀ ችሎታ ያለው አድርገው ያዩታል፡፡ አባላቶቹ አገሪቱ የጣለችባቸውን ሃላፊነት በታማኝነት ለማስፈጸም ሃላፊነት እንዳለባቸው ያምናሉ፡፡[24] በዚህ ጥሩ ሰው የተነሳ፣ የቦተስዋና መከላከያ ሃይል የመመልመል ችሎታ ከፍተኛ ነው፡፡ በየጊዜው በአመላመል ሂደቱ ጥንቃቄና መራጭነቱ ጨምሮዋል፤ የሚፈልገውን ተቋማዊ ባህል ለመፍጠር በስነምግባር የታነጸ፣ የተማረና ብቃት ያላቸው መሪዎች፣ በ 2004 የቦተስዋና መከላከያ ሃይል ከ 80-100 ዕጩ መኮንኖች ለመመልመል ፈለገ፡፡ ለዚህም ወደ 3,000 የተወዳዳሪ ማመልከቻዎች ተቀብልዋል፡፡ 500 ተራ ወታደር ለመመልመል ፈልጎ 15,000 አመልካቾች ፍላጎት አሳይቶዋል፡፡”[25]

በፖለቲካ ሂደት ውስጥ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ለማስቀረት በአህጉር ደረጃ ትርጉም ያላቸው ማስተካከያ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ከነዚህ መዋቅሮች ውስጥ፣ የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ የጋራ መከላከል እና ጸጥታ ፖሊሲ፣ የአፍሪካ አንድነት ምላሽ ለኢህገመንግስታዊ ለውጦች፣ የደቡብ አፍሪካ የእድገት ማህበረሰብ የስትራቴጂያዊ ማመልከቻ እቅድ ለፖለቲካ፣ መከላከያ፣ እና ደህንነት ትብብር፣ የምእራብ አፍሪካ አገሮች ኢኮኖሚ ማህበረሰብ (ኢኮዋስ) የታጠቁ እና የደህንነት ሃይሎች የስነ ምግባር መመሪያ፤ የእነዚህ አዝጋሚ ግልጽ የሆኑ አህጉራዊ መርሆዎች የሚያሳዩት እያደገ የመጣውን የአህጉሩን ወታደራዊ ክህሎት የተላበሰ ተቋም አስፈላጊ እየሆነ መምጣቱን ያሳያል፡፡ በተግባር ላይ ከዋለ፣ እነዚህ መመሪያዎች ለአፍሪካ እድገት ስር ነቀላዊ ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

# የወታደራዊ ሙያ ክህሎት በአፍሪካ መሰናክሎች

## የቅኝ ግዛት ውርስ

የመጀመሪያው መነሻ ነጥብ፣ ለምን የአፍሪካ ጦር በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጣልቃ እንደሚገባ ስሩ ያለው በአህጉሩ የቅኝ ግዛት ታሪክ ውስጥ ነው፡፡ ከፈራረሰው የቅኝ ሃይል በመንገባቱ በቅኝ ገዢዎች የተዘራውን የብሔር ማበላለጥ የአፍሪካ ሚሊታሪ ለመውረስ ተገድዋል፡፡ ያም አሁን ለሚታየው የሙያዊ ክህሎት ማነስ መንገድ ጠርጓል፡፡ በግልጽ እንደሚታየው፣ በቅኝ ግዛት ጦር ሃይል ውስጥ አናሳ ብሄሮች አብዛኛውን ቁጥር ይሸፍናሉ፡፡ ይህም በታሪክ ጉልበተኛ የነበሩትን ብሄሮች ተጽእኖ ለመቀነስ የታሰበ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የቱትሲ አናሳ ብሄር በቡሩንዲና ሩዋንዳ፣ በከብት ማርባት የተሰማሩት አናሳ ብሄረሰቦቹ በጋና፣ ናይጄሪያና ቶጎ በአብላጫ መልኩ በፈረንሳይና በእንግሊዝ የቅኝ ግዛት ሃይል ውስጥ ተሰማርተው ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ እስከ ቅኝ ግዛት ማብቂያ ቀጥልዋል፡፡

ይህ የብሄር አድልዎ የተከተለ አሰራር ከነጻነት በሁዋላ ለሚቋቋመው የጦር ሃይል ፈታኝ ሆንዋል፡፡ ከነጻነት መመለስ በሁዋላ የተካሄዱት በርካታ መፈንቅለ መንግስቶች የተገበሩት ከዚሁ ከአናሳ ብሄረሰቦች በሚወከሉ ወታደራዊ መኮንኖች ነው፡፡ ዝናን ካተረፉ መሪዎች ውስጥ፣ ኤትየን ኢያዴማ ከቶጎ 1963 ፣ ሳንጉሌ ኢያሚዛና ከቡርኪና ፋሶ አሁን አፐር

ቮልታ በመባል የምትታወቀው በ 1966 ፣ ጂን ቤዴል ቦካሳ ከመካከለኛው አፍሪካ በ 1966 ፣ ኢዲ አሚን ዳዳ ከዩጋንዳ በ 1971 ይገኙበታል፡፡ ያላቸው የበላይነት በብዙሃኑ አገዛዝ ስር እንደሚነጠቅ በመገንዘብ፣ በአናሳው ብሄር የሚመሩት የጦር ሃይሎች ለለውጥ የሚያነሳሳ ምንም ምክኒያት አይኖራቸውም፡፡ በዚህ አኳያ፣ ቅኝ ገዢዎች የአፍሪካን መኮንኖች ለለውጥ ለማዘጋጀት የሚያነሳሳ ፋይዳ አልታያቸውም፡፡ በዚህም የተነሳ፣ በቂ ችሎታ ያላቸው መኮንኖች በአመራር ላይ አልነበሩም፡፡

ከ 50 አመት በሁዋላ፣ የአፍሪካ ጦር ሙያዊ ክህሎት ማነስን በቅኝ ግዛት ዘመን ስሕተት ማሳበብ ልክ አይሆንም፡፡ በአፍሪካ ልጆች የሚመሩት መንግስታት በቂ እድል ነበራቸው፡፡ አዲስና እውነተኛ ብሄራዊ ጦር ለመገንባት ማድረግ የሚጠበቅባቸውም ከቅኝ ገዥዎች የተወረሰውን መዋቅር፣ የስራ አፈጻጸምና የመመልመል አካሄዶች መቀየር ነው፡፡ በአንጻሩ ግን፣ ከነጻነት በሁዋላ የመጡት መሪዎች እነዚህን የተበላሹ አሰራሮች የራሳቸውን አምባገነን ስርኣት ለማቆየት ተጠቅመውበታል፡፡ ይሄም፣ ለአፍሪካ ወታደራዊ ሙያ ክህሎት ማደግ በርካታ ፈታኝ ሁኔታዎችን ፈጥሮዋል፡፡ ከዚህ ጋር አብረው የሚነሱትም ችግሮች ውስጥ፣ የብሄርና የዘር አድልዎ በጦር ሃይል ውስጥ የጦሩ ያለማቋረጥ ከፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ መዘፈቅና የስራ አፈጻጸም ብቃት ማነስን ይጨምራል፡፡

## የብሄር እና የጎሳ መድልዎዎች

በጎሳና በዘር አድልዎ ላይ የተመሰረተ የጦር ሃይል መላ ሃገር መከላከል አይቻለውም፡፡ የራሱን ዘርና ጎሳ አባላት ጥቅም ብቻ ነው የሚያስከብረው፡፡ የህዝብ አመኔታ፣ ህጋዊነትና የሙያ ብቃት አይኖረውም፡፡ ይህም የጦሩን ውጤታማነት ያደናቅፋል፡፡ እንዳለመታደል፣ በብዙ የአፍሪካ አገሮች፣ የመከላከያ ሃይል አወቃቀር ዘርና ጎሳን ያማከለ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ የሞሪታኒያ ጦር ሃይል በዘር፣ በጎሳና በባህል የተከፋፈለ ነው፡፡ አንድ ሰስተኛ የሚሆነው፣ የአረብ በርበር ብሄር ፖለቲካውን፣ ኢኮኖሚያዊውንና ወታደሩን ከነጻነት ጀምሮ በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡[26] ከ 1987 ቱ የዘር ተኮር መፈንቅለ መንግስት ሴራ በሁዋላ፣ የሞሪታኒያ ፕሬዚደንት፣ ኡድ ታያ፣ ሁሉንም የጦር ሃይል ዘርፎች ወደ አረባዊነት ለመቀየር የሚያስችል ፕሮግራም ተግባራዊ አደረገ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በቻድ የመከላከያ ሃይሉ የብሄር ስብጥር የአገሪቱዋን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያንጸባርቅ አይደለም። ዛግ ሃዋስ፣ የፕሬዝደንት ኢድሪስ ዴቢ ብሄር፣ የጦሩን ከፍተኛ ስልጣኖች በሙሉ በስሩ አድርጓል። ይህም ሁኔታ ከ 1990 ፕሬዚደንት ሂሴኔ ሃብሬን ከስልጣን ካስወገዱ ጀምሮ ነው። ሌላ ምሳሌ የሚሆን ጦር ሃይል ደግሞ የቶጎ መከላከያ ሃይል ነው። 77 % የሚሆነው የጦሩ ክፍል ከሰሜኑ ክፍል በመጡ ሰዎች የተሞላ ነው። ከነዚህ ውስጥ 42 % ብቻ ነው የሚወክለው። 70 % የሚሆኑት ካቢየን ናቸው። ፕሬዝደንቱም የዚህ ጎሳ አባል ናቸው። 50 % የሚሆኑት የመጡት ፕሬዝደንቱ ከተወለዱበት ክልል ፒያ መንደር ነው። ይህም ማለት፣ የካብያ ጎሳ ከአጠቃላይ የቶጎ ህዝብ ከ 10-12 % ብቻ ነው የሚወክለው።[27]

በአፍሪካ የጦር ሃይሉን ፕሬዝደንቱ ከሚወለዱበት ቦታ በአብላጫ ሁኔታ መመልመል የተለመደ አሰራር ነው። በእንደዚህ አይነት የዕዝ ሰንሰለት፣ የጦር መኮንኖች ከህገ መንግስቱ ይልቅ ታማኝነታቸው ለፕሬዝደንቱ ነው። ይህ አካሄድ፣ የጦር ሃይሉን የዘር ሽኩቻ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ የጦሩ ብቃት ማነስን ይፈጠራል። እንደዚህ አይነቱ ክፍፍል፣ ድንገተኛ ብጥብጥ ሲነሳ በገሃድ ይወጣል። በታህሳስ 2013, በደቡብ ሱዳን እንደታየው፣ የዛችን ጀማሪ ሃገር የጸጥታ ተቋም ምስረታ ጥረት ወደ ሁዋላ እንዲመለስ አድርጓል።

በአንጻሩ ከመላው የሃገሪቱ ክፍል የተዋቀረ የጦር ሃይል፣ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት የሚያስችል አስተማማኝ ሁኔታ ይፈጥራል። ሁሉን አቀፍ የሆነ የጦር ሃይል እድገት ዘርን መሰረት ያደረገ ሳይሆን፣ በችሎታ ስለሚሆን፣ የሙያ ክህሎቱን የጠበቀ ጦር ለመመስረት ይረዳል። እንዲሁም፣ ወገናዊነቱ ለጠቅላላ ለሃገር እንጂ ለአንድ ወገን ብሄር አይሆንም። እንደ ምሳሌ ሊቆጠር የሚችል፣ ሁሉን አቀፍ የሆነና፣ የጠቅላላ ሀገሪቱዋ ነጸብራቅ የሆነ ወታደራዊ ሃይል የሚገኘው በታንዛኒያ ነው።

የ 6ተኛው ባታሊዮን የንጉሱ አፍሪካዊ ጠመንጃዎች በእንግሊዞች ሲመሰረት፣ በአንደኛ አለም ጦርነት ማብቂያ ላይ፣ ወታደሮች የተመለመሉት ከሁሉም ብሄሮች ሲሆን ሙሉ ሃገሪቱን ባማከለ መልክ ነበር። ይህ ሁኔታ ጸረ እንግሊዝ የሆነውን የጀርመን ቅኝ ገዢ ጦር ይጨምራል። አንድ የበላይ የሆነ ጎሳ አልነበረም።[28] ታንዛኒያ፣ በጊዜው ታንጋኒካ ተብላ ነበር የምትታወቀው፣ ለቅኝ ግዛት የተመቻቸች ስላልነበረች እንግሊዞች በዘር የተከፋፈለ ጦር ለመመስረት ጥረት አላደረጉም።[29] ነጻነት እንደተገኘ፣ የታንጋኒካ የመጀመሪያ

ፕሬዝደንት፣ ጁሊየስ ኔሬሬ፣ ጦሩን የቅኝ ግዛት መጨቆኛ መሳሪያ አድርጎ ስለተመለከተው፣ ሆን ብሎ እራሱን ከጦሩ አሸሸ። ታንጋኒካና ዛንዚባር ተዋህደው ታንዛኒያን ፈጠሩ። በ 1964 የጦሩ ሃይሉ ደሞዝ ይጨመርና የእንግሊዝ መኮንኖች ይውጡልን አድማ ድረስ ኔሬሬ ሃሳቡን አልቀየረም ነበር። አከታትሎም፣ አፍራሽ የሆነ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት እንዳይፈጠር በማሰብ ብሄራዊ ማንነት ያለው ጦር ለመፍጠር ተነሳ።[30]

በተመሳሳይ፣ እንግሊዞች በዛምቢያ፣ ሰሜን ሮዴዢያ ተብላ በጊዜው በምትታወቀዋ፣ ወታደራዊ ምልመላው ከመላው ሃገሪቱ ሁሉንም ብሄሮች ያቀፈ አካሄደዋል። በዚህም የተነሳ፣ በዛምቢያ ጦር ሰራዊት የአንድ ጎሳ የበላይነት አልነበረም። ከኔሬሬ በአንጻሩ፣ የወደፊቱ ፕሬዝደንት፣ ካውንዳ፣ ከቅኝ ገዥው ጦር ውስጥ ያሉ የአፍሪካ መኮንኖች ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረው። በዚህም የተነሳ፣ በ 1964 ፣ ዛምቢያ ነጻነትዋን ስትቀዳጅ በወታደሩና በሲቪሉ መካከል አለመተማመን አልነበረም። ከነጻነት በሁዋላ፣ በጎሳዎች መካከል መመጣጠን የሚያስችል ፖሊሲ ተከትሎዋል። በሁሉም የመንግስት ተቋሞች የተገበረ ነበር። ሚዛኑን ያልጠበቀ የብሄር አደረጃጀት ለወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ከሰሃራ በታች ላሉ የአፍሪካ ሀገሮች እንደምክኒያት መሆኑን የካውንዳ ፖሊሲ ያገናዘበ ነው።[31]

ሁሉን አቀፍ ዘመናዊ ምሳሌ የሚሆነን የደቡብ አፍሪካ መከላከያ ሃይል ነው። ከቅኝ ግዛት ማብቃት ተከትሎ፣ በተቀናጀ ጥረት፣ በተለያዩ በጠላትነት ከሚተያዩ ሃይሎች ውስጥ ጦር መመስረት ተችሎዋል። በፖለቲካ ሽግግር ውስጥ በሚፈጠሩ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ተቋሙ እራሱን በመለወጥ የጠቅላላ የደቡብ አፍሪካ ነጸብራቅ ለመሆን ችሎዋል። የደቡብ አፍሪካ ብሄራዊ የደህንነት ፖሊሲ አካል በመሆን፣ መንግስት፣ ጦሩ፣ እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰቡ ተቀራርበው በመስራት ላይ ናቸው።

የቡሩንዲ ጦር፣ የቡሩንዲን አጠቃላይ ህዝብ ነጸብራቅ እንዲሆን በማሰብ፣ ኮታ መሰረት ያደረገ ምልመላና አስገዳጅ የጡረታ መውጫ ጊዜ ደነገገ። በጠንካራ አመራር ስር፣ ከ 2003 ተኩስ ማቆም ስምምነት በሁዋላ፣ የሁቱ ተዋጊዎችን ብዙሃኑ ቱተሲ በሆኑበት መደበኛ ጦር ጋር ለማዋሃድ ስራ ተጀመረ። የማዋሃድ ስራው በሁሉም የጦር ክፍል ውስጥ የተካሄደ ሲሆን፣ ከተለያየ የጎሳና የዘር ቅኝት የመጡ ወታደሮች በአንድ በታና ምሽግ ልምምድ እንዲወስዱ ተደረገ። በሶስት አመት ተኩል ውስጥ ዘር ተኮር በደሎች በከፍተኛ ደረጃ ቀንሰው ታይተዋል። በተለይም በወጣት

ወታደሮች መሃከል፡፡ በዚህም የተነሳ፣ የቡሩንዲ ጦር ውህደትና መስማማት የሚታይበት ሆኖዋል፡፡[32]

## የወታደሩ ፖለቲካዊ ማንነት መዳበርና የፖለቲካው ወታደራዊ ስብእና መውሰድ

የወታደሩ የፖለቲካ ተዋናይ መሆን፣ ባብዛኛው በፖለቲከኞቹ መካከል የወታደሩን ድጋፍ ለማግኘት የሚደረገው ፉክክር ለመደበቅ ረድትዋል፡፡ እንደሚታየው፣ በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ መፈንቅለ መንግስት ሂደቶች፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ሃይሎች ሲደግፉት ተስተውልዋል፡፡ እነዚህ ተጻራሪ ሃይሎች በገዢው ፓርቲ ውስጥ ሲከሰቱ፣ አጠቃላይ ህገ መንግስታዊ ስርኣቱን የሚያፈርስ ሁኔታ ሳይፈጠር በአንጻሩ የቤተ መንግስት አብዮት ነው የሚሆነው፡፡ በቶጎ፣ ለምሳሌ፣ ፕሬዝደንት ናሲንግቤ አያዴሜ፣ በ 2005 ሲሞት፣ ለፕሬዝደንቱ ታማኝ የሆኑ ጄኔራሎች፣ የፕሬዝደንቱን ልጅ ፋአሬ ናሴንግቤን ቦታውን እንዲይዝ አድርገዋል፡፡ ምንም እንኳን ህገ መንግስታዊ መብት ያለው የጠቅላላ ምክር ቤቱ ሊቀመንበር ቢሆንም፡፡

አንዳንድ ፖለቲካ ፓርቲዎች በቀውስ ጊዜ ስልጣን ለመያዝ እንዲያመቻቸው በማለት ከጦሩ ክፍል ደጋፊ ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ ለመናገር ያህል፣ የ 2012 ወታደር የማሊ የወታደሩ መፈንቅለ መንግስት ከተለያዩ የፓለቲካዊ ፓርቲዎች ድጋፍ ሲያገኙ ከአለም አቀፍ ማህበረሰቡ ውግዘት ደርሶባቸዋል፡፡ በኮት ዲቭዋር፣ የቀድሞው ፕሬዝደንት ሎረን ባግቦ ታማኝ ተከታዮች፣ የፕሬዝደንት አላሳኔ ኡታራን መንግስት ስልጣን ለማዳከም፣ የጦሩን ክፍል እርዳታ ለማግኘት ይንቀሳቀሳሉ፡፡[33] ይህ የፖለቲካና አርሚ የተወሳሰበ ግንኙነት የተለመደ የአፍሪካ መገለጫ ነው፡፡ ፖለቲከኞች በህዝብ ድጋፍ ላይ ሳይሆን እምነታቸውን የጣሉት በወታደሩ ክፍል ላይ ነው፡፡

ምንም እንኳን ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የወታደራዊ ሙያ ክህሎት፣ በተወሰኑ የምእራብ አገሮች፣ ፖለቲከኞች ለግል ጥቅማቸው የጸጥታውን ክፍል ማዞር ያረጀ ያፈጀ ሃሳብ ቢሆንም፣ የወታደሩን ክፍል ወዳጅነት ለማግኘት የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም በአፍሪካ የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አካሄድ በመሰረቱ አስተማማኝ አይደለም፡፡ ይህም በኮት ዲቭዋር ተሞክሮ በግልጽ ታይቶዋል፡፡ የመጀመሪያው የኮት ዲቭዋር ፕሬዝደንት ፌሊክስ ሁፌት ቡዋኘ፣ የጸጥታውን ዘርፍ ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠረ ጊዜ፣

የአርሚውን መጠን አሳንሶ፣ በባውሌ ብሄር የተሞላ፣ ለፓርቲው ብቻ ታማኝ የሆነ ሚሊሽያ አቋቋመ፡፡ ባውሌ ጎሳ የፕሬዝደንቱ ጎሳ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ወታደራዊ መኮንኖችን ከሲቪሉ ሰራተኛ የበለጠ ደሞዝ መክፈል፣ በፓርቲ ውስጥ መኮንኖችን በታ መስጠትና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የመስጠት አካሄድ ተከትሎዋል፡፡[34]

ይህ አድልዎ የተሞላው ልግስና ወደፊት ለተከሰተው የኮት ዲቭዋር አለመረጋጋትና የጸጥታ ችግር መንገድ ቀዳጅ ሆኖዋል፡፡ በ 1993 ፣ ሁፌት ቡዋኘ ሲሞት፣ የአጠቃላይ ምክር ቤቱ ፕሬዝደንት፣ ሄነሪ ኮናን ቤዲዮ፣ ከራሱ ጎሳ በመጡ ጥቂት ወታደሮች በመታገዝ፣ ስልጣን በጉልበት ያዘ፡፡ በዚህም የተነሳ፣ በኮት ዲቭዋር፣ ፖለቲካዊና ህገ መንግስታዊ ታሪክ ባልተለመደ ሁኔታ፣ የጸጥታው ሃይል የነበራቸውን ውህደትና በፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት ዝንባሌያቸውን ወደ ጎን በመተው፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ዋነኞቹ የፖለቲካ ጨዋታ ተሳታፊዎች ሆኑ፡፡[35] ይሄው ጦር፣ የተሻለ ትጥቅ፣ የተሻለ ልምምድ፣ ከቀረው የአይቮሪያን ጦር ሃይል ጋር ሲነጻጸር ነበረው፡፡ በ በተደረገው ምርጫ፣ ላውረንት ጋግቦን ወደ ስልጣን መንበር እንዲመጣ አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን ጄኔራል ሮበርት ጉኤ፣ ሌላኛው የምርጫ ተፎካካሪ አሸንፌያለሁ ቢሉም፣ እንደ ሌሎች የአፍሪካ ሃገሮች፣ በጸጥታው ሃይል ውስጥ ያሉ ሃይሎች መሪ አውጪና አውራጅ ሆነው ቀጥለዋል፡፡

የዚህ አይነት ትስስር የሚያስከትለው ውጤት፣ በህዝብ አይን ወታደሩ ወገንተኛ እና ሙያዊ ክህሎት ያነሰው እንዲሆን አድርጓል፡፡ አክብሮት በመቀነስ የተነሳ፣ ተሰጥኦ ያላቸውንና በስነ ምግባር የታነጹ ወታደሮች ለመመልመል ያለውን ችሎታ ቀንስዋል፡፡ የወታደሩን ድጋፍ የማግኘት ፍላጎትም ነው፡፡ ፖለቲከኞች የጦር መሪዎች የህዝብ ንብረት ለግል ጥቅም ሲያውሉ ታጋሽነት የሚያሳዩት፣ አልፎ አልፎም የሚያበረታቱት፡፡ ይህ እውነታ የሚያመለክተው፣ የወታደሩን ክፍል ፖለቲካዊ ሚና ተጫዋችነት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካውንም ወታደራዊ ሚና ተጫዋችነት ያሳያል፡፡

## የፕሬዚደንት ልዩ ጥበቃ በዲሞክራሲያዊ ያልሆኑ አገዛዞች ጀርባ ያለ ሃይል

የፕሬዝደንቱ ልዩ ጥበቃ በአፍሪካ ፖለቲካ ትልቅ ሚና ተጫዋች ነው። በቡርኪና ፋሶ፣ 2011 በነበረው አመጽ፣ የፕሬዝደንቱ ልዩ ጥበቃ በአድማው መሳተፍ እስኪጀምሩ ሁኔታው ከቁጥጥር ውጪ አልነበረም። በውጤቱም፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ቴሪትየስ ዞንጎና መንግስቱ ከስልጣን እንዲለቁ ተገደዱ፣ ቁልፍ ቦታ ላይ ያሉ ወታደራዊ መሪዎች ተባረሩ፣ ያመጸኞቹ ጥያቄም በከፊል ተመለሰ። ጥያቄያቸው ከተመለሰ በሁዋላ፣ ይሄው የፕሬዝደንቱ ልዩ ጥበቃ ሃይል በመጠቀም የሌሎች ወታደሮች አድማ እንዲቆም አድርጓል።

የቡርኪና ፋሶ ክስተት የሚያሳየው፣ በአፍሪካ የመንግስት ደህንነትና መረጋጋትን በተመለከተ የፕሬዝደንቱ ልዩ ጥበቃ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ነው። በተግባር፣ የፕሬዝደንት ልዩ ጥበቃ ሃይል ከሌላው መከላከያ ሃይል በተነጻጻሪነት ሚዛን የመጠበቅ ሚና አለው። በዚህም፣ በመፈንቅለ መንግስት በማካሄድም ሆነ በማክሸፍ ትልቅ ሚና ይጫወታል። በአፍሪካ በሞሪታኒያ፣ ፕሬዚደንት ጄኔራል ኡልድ አብደል አዚዝ የራስ ገዝ ፕሬዚደንታዊ ደህንነት ባታሊዮን (ቢኤኤስኢፒ) ከ 15 አመታት በላይ መርቶዋል። ይህንን የሞሪታኒያ ሰራዊት የተመረጠ ክፍል ሲመሩም፣ በ 2008 አንዱን የራሱን መፈንቅለ መንግስት ከማድረግ በፊት ሁለት መፈንቅለ መንግስት አክሽፎዋል። በብዙ የአፍሪካ ወታደሮች፣ ስለዚህም እውነተኛ ሃይል በፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ እጅ ስር ነው ማለት ነው።

ፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ በአጠቃላይ የተሻለ የታጠቁ፣ የሰለጠኑ፣ እና የሚመሩ፣ ይህም ከተቀሩት የሰራዊቱ ሃይሎች ጋር ሲነጻጸር ማለት ነው። የፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ በመከላከያ ሚኒስትሩ ወይም በጦር ሃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ስለማይቆጣጠሩ፣ በሰራዊት ውስጥ ያሉ ሰራዊት ተደርገው ይወሰዳሉ። ብዙውን ጊዜ በጣም ፖለቲከኛ የሆኑና የጎሳ አድሎ ያለባቸው ናቸው። በሌላ ቃላት፣ የአፍሪካ ጦር ሃይሎች ሙያዊ ብቁ አለመሆን ምልክቶችን በሙሉ ሲያሳዩ፣ ከፖለቲካ ሃይል ሲነጻጸር የበለጠ ወሳኝ ናቸው። ስለዚህም፣ የፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ ባለስልጣናት የደካማ ደህንነት ሴክተር አመራር ምንጭ ናቸው። ያላቸውን ወሳኝ ሚና ለመጠበቅ፣ እነዚህ የፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ ይህንን ከፍተኛ ስልጣን ለሚጻረር ማንኛውም ለውጥ እና መሻሻል ተቃዋሚ ናቸው። በሃገሪቱ መሪ ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር ስለሆኑም፣ ለተቀረው የጦር ሰራዊት እንደመመከቻ ሆነው ይሰራሉ።

አንዳንድ ፕሬዚደንታዊ ክቡር ዘበኛ የአፍሪካን መንግስታት በጭቆና ሃያላቸውን እንዲያቆዩ ረድቶዋል። በ 2012 ምርጭዎች በዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኮንጎ፣ ለምሳሌ፣ የፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ ቁልፍ የተቃዋሚ መሪዎችን በማሰር የሂደቱን ታማኝነት አሳጥቶዋል። በመጨረሻም፣ በጭቆና መምራት አያዛልቅም። ይልቁንም፣ እነዚህ ተግባራት የህዝብን እምነት እና የተቋሙን ታማኝነት መንግስቱ እስከሚፈርስበት ጊዜ ድረስ ያሳንሳሉ። በኒጀር የተከሰተውም ይህ ነው። በ 1999 ፕሬዚደንት ኢብራሂም ባሬ ማይናሳራ

በፕሬዚደንታዊ ክቡር ዘበኛ ተገደለ። የክቡር ዘበኛው መሪ፣ ሻለቃ ዳዉዳ ማላም ዋንኬ፣ አገሪቱዋን ተቆጣጠረ። ከምርጫዎች በሁዋላም የጦር ሰራዊቱ ባለስልጣን በፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ ተደግፎ ወደ ስልጣን ወጣ። ከአስር አመታት በሁዋላ፣ ፕሬዚደንት ታንጃ በመፈንቅለ መንግስት፣ ታማኝ ሆኖ በቆየው ፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ ሳይሆን፣ በሰራዊቱ ሻለቃ ሳሉ ዲጂቦ፣ ታንጃ መንግስቱን አግዶ በራሱ ፈቃድ መምራት እንደሚጀምር ሲያሳውቅ፣ ከስልጣን ተወግዶአል።

ሃይላቸው በመራሂ መንግስቱ ላይ መመርኮዙን በመረዳት፣ ብዙ የፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛዎች በአፍሪካ ለመሪያቸው ታማኝ ሆነው ይቆያሉ፤ አካሄዱ ከህገ መንግስት ውጭ ቢሆንም እንኳን። በአጠቃላይ የተገደቡ መስሎ ስለማይሰማቸውም፣ በብሄራዊ ደህንነት ስር ለሚካሄዱ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች የህግ ተጠያቂነት አያሳስባቸውም። በጊኒ፣ ለምሳሌ፣ በ 2009 ወታደራዊ ቡድን መሪ ሻምበል ሙሳ ዳሪስ ካማራ ላይ በተካሄዱ የተቃውሞ ሰልፎች፣ ባልታጠቁ ተቃዋሚዎች ላይ በብሄራዊ ስቴዲየሙ ላይ ተኩስ ከፍተው የደም ጎርፍ አምጥተዋል። ቢያንስ 157 ሰዎች ሲገደሉ፣ ወደ 1,200 አካባቢ ቆስለዋል፤ እንዲሁም ቢያንስ 63 ሴቶች ተደፍረዋል።[36] በሁዋላም፣ ካማራ ራሱ በፕሬዝደንታዊ ክቡር ዘበኛ መሪ ከተነሳሳ የግድያ ሙከራ ደርሶበታል።

## ደካማ የአሰራር ብቃት፣ አላማ የሌላቸው ወታደሮች ምልክት

የወታደሩ ሙያዊ ብቃት የሚተማመነው በትክክለኛ የትእዛዝ እና የቁጥጥር ሲስተሞች፣ ክህሎቶች፣ እና ውጤታማ አላማዎችን ለማሳካት ሃብቶች ላይ ነው። በብዙ የአፍሪካ ወታደሮች ደካማ የአሰራር ብቃት ይህንን ሚና እንዳይጫወቱ አድርጎዋል፤ ይህም አስፈላጊነታቸውን ጥያቄ ውስጥ ከቶዋል። የማሊ ወታደሮች በእስላማዊ ነውጠኞች በ 2012 መባረር፣ የጎማ አሁን በፈረሰው ኤም23 አማጺ ቡድን በዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኮንጎ በዛው አመት መያዝ፣ እና የመሃከለኛው አፍሪካ ሪፑብሊክ ወታደር መበታተን የሴሌካ አማዚ ሃይሎች በ 2013 ባንጉይን በቀላሉ መያዝ፣ እነዚህ የብዙ ከሰሃራ በታች ወታደሮች ደካማ የአሰራር ብቃት ማሳያ ናቸው። ይህንን አለመብቃት ከሚያሳዩ ምክኒያቶች አንዱ፣ የሚከተሉት ነጥረው ይወጣሉ፤ በእዝ ሰንሰለት ላይ ያሉ ክፍተቶች ወደ ስነ ምግባር ጉድለት፣ በግዢ ልምዶች ላይ በቂ ያልሆነ ክትትል፣ ደካማ የሃብት አስተዳደር የአሰራር ብቃትን ማሳነሱ፣ ደካማ ሞራል፣ እና ያልተዛመደ ወይም ጊዜው ያለፈበት አላማ ናቸው።

**በእዝ ሰንሰለት ላይ ያሉ ክፍተቶች ወደ ሞራል ማጣት መምራት** ለማንኛውም የወታደር ተቋም በቅድሚያ የሚያስፈልገው የስራ የእዝ ትእዛዝ ነው። የሚያመለክተውም ጥሩ የአመራር እና ዲሲፕሊን እንዲሁም ተጠያቂነትን ነው። እንዳለመታደል ሆኖ፣ ከአፍሪካ የሚወጡት ሪፖርቶች የሚያሳዩት ስእል ግራ እጅ ቀኝ እጅ የሚያደርገውን እንደማያውቅ ያህል ነው። በወታደር ፖሊሲ እና ከስር ባለው ሰራተኛ ያለው በጣም ትንሽ ግንኙነት ነው ያለው። አንድ ማሳያ ምሳሌ በሰሜን ናይጄሪያ ወታደሮቹ ቦኮ ሃራም ተዋጊዎችን ሲዋጉ በሲቪል ማህበርሰቡ ላይ ጥቃቶችን በማድረስ ተከሰዋል።[37] የበላይ የናይጄሪያ ወታደር መሪዎች እነዚህን ድርጊቶች ማስተባበል አቅቶዋቸዋል፤ ምንም እንኳን የከባድ የአገር ውስጥ የደህንነት ስራዎች በአካባቢው ህዝብ ላይ ያለውን ተጽእኖ ቢረዱም።

ባብዛኛው የአፍሪካ ወታደሮች የሚመሩት በተጻፉ ህጎች ነው፣ እንደ የታጠቁ ሃይሎች ሰራተኞች መመሪያዎች እና የወታደር ዲሲፕሊን ኮድ። ሆኖም፣ የወንጀል ድርጊቶች ከግድቡ ውጪ ያሉት በእዝ ሰንሰለት እና በዲሲፕሊን ቦርዱ ባሉ ክፍተቶች የተነሳ ሳይቀጡ ይሄዳሉ፤ ይህም ወታደሩ በአንዳንድ አገሮች ከህግ በላይ ነው የሚል ምልከታ ያመጣሉ። ይህም የጥፋት ባህልን ሲያበረታታ የወታደሩን ዝና ዝቅ በማድረግ በሰራዊቱ መሃል ጋጠ ወጥነት ያበረታታል።

በኮት ዲቭዋር ውስጥ በላውሬንት ግባግቦ ስር፣ በ 2000—ላይ የነበረውን ጭፍጨፋ ያነሳሱት ላይ ምንም ማእቀብ አልተካሄደም፤ የግባግቦ ታማኝ ደጋፊዎች የግባግቦን መመረጥ ጥያቄ ውስጥ ለከተቱ ሰዎች ላይ ግድያ ፈጸሙ። እንዲሁም በ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የነበሩ ግድያዎች ላይ ተጠያቂነት የለም። በ 2004 የአላሳን ኦታራ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ስልጣን ላይ ሲወጣ፣ አነሳሾቹ ተፈርዶባቸዋል። ሆኖም፣ የኦታራ መንግስት በአከራካሪው የየአላሳን ኦታራ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ስልጣን ላይ ሲወጣ፣ አነሳሾቹ ተፈርዶባቸዋል። ሆኖም፣ የኦታራ መንግስት በአከራካሪው የ 2010 ምርጫ ማግስት የተፈጸመውን ወንጀል እስካሁን አልተጠየቁም።

በርግጥ አንዳንዱ ልዩ ተሞክሮዎችም አሉ። በቤኒን፣ በተለያየ ጊዜያት ያሉ ፍርድ ቤቶች ከገንዳመሪው መርማሪዎችን እንዲሁም በፖሊስ ቁጥጥር ስር ያሉትን ዜጎች በህገወጥ መንገድ ማሰር እና ማሰቃየት ላይ የተሳተፉ ፖሊሶችን አስሮዋል። በቡርኪና ፋሶ፣ 566 ወታደሮች በ ሙቲኒ

የተሳተፉት ከሰራዊቱ ተባረሩ፤ እንዲሁም 2011 217 የሙቲኒው መሪዎች ታሰሩ፣ በወታደራዊ ፍርድ ቤት ተከሰሱ፣ እናም የታጠቁ ሃይሎችን ክብር በመንካታቸው፣ የህዝብ ስርኣተ አልበኝነትን በማምጣት፣ እና የሰብአዊ መብቶችን በመጣስ የተነሳ ታስረዋል፡፡[38]

**የግዢ አሰራሮች በቂ ያልሆነ ክትትል** ሌላው የወታደሩ ደካማ አመራር ማሳያ ለሃይሎቹ የቁሳቁስ እና መሳሪያ ግዢ ነው፡፡ በአብዛኛው ወታደሮች እንደሚያማርሩት የሜዳ ህይወት አስቸጋሪ እንደሆነ፣ ክፍያው ኢምንት እንደሆነ፣ እና ለማደግ ያለው እድል ምንም እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን፣ ለወታደሩ ያለው በጀት ከሌሎች የህዝብ አገልግሎቶች በላይ ነው፡፡ በናይጄሪያ፣ ለምሳሌ፣ ብዙ ወታደሮች በሜዳ ውስጥ ያሉት እስካሁን የሚኖሩበት ሁኔታ ጥሩ አይደለም፤ ምንም እንኳን በወታደሩ ላይ ኤን12 ቢሊዮን (ወደ $76 ሚሊዮን) በሜዳ ሰፈር እደሳ እና ግንባታ ላይ ቢውልም፡፡[39] የሙስና ክስ ከጊዜው ካለፈበት መሳሪያ ግዢ እና የቁሳቁሶች ወደ ቦኮ ሃራም መሄድ በናይጄሪያ ወታደር ላይ ያለውን እምነት የበለጠ ሲሸረሽረው ብቃቱንም ቀንሶታል፡፡

ለዚህ አለመገናኘት አንዱ ምክኒያት የመከላከያ የገንዘብ ነክ እና አስተዳደር ጉዳዮች ክፍል የተለመዱ ባዶ ቀፎዎች ናቸው፤ በጣም በቂ ሰራተኞች የሌሉዋቸው እና ስራቸውን ለማስፈጸም መንገዶች የሌሉዋቸው ናቸው፡፡ በዚህም ምክኒያት የመከላከያ ሚኒስትሪዎች የግዢ ስምምነቶችን በደንብ አለመቆጣጠራቸው የተስፋፋ ሙስና እና የአስተዳደር ችግር ፈጥሮዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በ 19 የአፍሪካውያን የመከላከያ ሴክተሮች፣ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ያገኘው 90 በመቶዎቹ ከታችኛው ሁለት ኳንታይል የግዢ አዙሪት (ሰንጠረዥ 2) ነው ያስመዘገቡት፡፡ ምንም እንኳን የአስተዳደር መመሪያዎች በመጀመሪያዎቹ የበጀት መስሪያ ሂደቶች ላይ ቢከበሩም፣ ከህዝብ የፋይናንስ ክፍሎች ቁጥጥር ለማምለጥ የሚያስፈልገው፣ ምስጢር ወይም የተሸፈነ የሚል ማህተም ጨረታዎቹ ላይ መኖር ነው፡፡ እንዲሁም አንዳንድ የወታደር ግዢዎች ለብሄራዊ ደህንነት ጥቅሞች ሲባል ምስጢራቸው የተጠበቀ ቢሆንም እንኳን፣ በአብዛኛዎቹ ይህ አያስፈልጋቸውም፡፡

## ሰንጠረዥ 2. በ 19 የአፍሪካ አገሮች በተመረጡ የመከላከያ ሴክተር የፋይናንስ እና የአስተዳደር ጉዳዮች የጸረ ሙስና ውጤቶች, 2013 (4=ከፍተኛ ግልጽነት, 0=ዝቅተኛ ግልጽነት)

| | ጸረ ሙስና ውጤት | በጀት ግልጽነት እና ዝርዝር | በጀት ማሰላሰል | በጀት ለህዝብ የሚገኝ | ውስጣዊ ቁጥጥር | ውጫዊ ቁጥጥር | የምስጢር ወጪ በመቶ | ህግ አውጪው መረጃውን ማግኘት መቻል | የምስጢር መርሃ ግብር ቁጥጥር | ከበጀት ውጪ ወጪ በህግ ውስጥ | ከበጀት ውጪ ወጪ በተግባር | የመረጃ በምስጢር መያዝ | ግልጽነት ያለው የግዢ ሂደት | የቁጥጥር ሂደቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኬኒያ | D+ | 2 | 3 | 0 | 1 | 1 | 0 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 0 | 1 |
| ደቡብ አፍሪካ | D+ | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 4 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| ኢትዮጵያ | D- | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 0 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| ጋና | D- | 2 | - | - | 2 | 2 | 0 | 1 | 2 | 0 | 1 | 1 | 1 | 3 |
| ሩዋንዳ | D- | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 2 | 0 |
| ታንዛኒያ | D- | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 0 | 2 | 2 | 0 | 2 | 1 | 1 | 2 |
| ኮት ዲቭዋር | E | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 1 | 0 | 0 | 2 |
| ሞሮኮ | E | 1 | 1 | 2 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 2 | 0 | 0 | 0 |
| ናይጄሪያ | E | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 2 | 2 | 2 |
| ቱኒዚያ | E | 1 | 0 | 1 | 0 | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 1 | 0 | 1 |
| ዩጋንዳ | E | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 0 | 1 | 2 | 0 | 0 | 1 | 1 | 2 |
| ዚምባቡዌ | E | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| አልጄሪያ | F | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 |
| አንጎላ | F | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ካሜሮን | F | 1 | - | - | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 0 | 1 | 1 |
| ዲአርሲ | F | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 1 |
| ግብጽ | F | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 |
| ኤርትራ | F | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 |
| ሊብያ | F | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | - | 1 | 0 | 0 | 0 |

ምንጭ፡ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የመከላከያ እና የደህንነት ፕሮግራም፣ 2013.[40]
የጸረ ሙስና ውጤቶች በ 77 የሙስና ስጋት ክፍልፋዮች ላይ የተመሰረተ ነው።

በብዙ አገሮች ወታደራዊ እቃ ግዥ ክፍሉ በጥቂት ወታደራዊና የፖለቲካ ንክኪ ባላቸው ክፍሎች እጅ የወደቀ ነው፡፡ ከሃገር ውስጥና ከውጪ የንግድ አካሎች ጋር ባላቸው የጥቅም ግንኙነት የእቃ ገዢ አፈጻጸሙ የጦሩን ፍላጎት ያገናዘበ ሳይሆ ለግል ሃብት ማከማቻነት ይውላል፡፡ በ 2007 ለወታደር የግዢ ጉቦ በአፍሪካ ወደ 10 የኮንትራቱን ነበር፡፡[41]

ቦና ለመደለያ የሚወጡ ወጪዎች ጦሩ የማያስፈልጉትን፣ የተበላሹና ከዋጋ በላይ የሆኑ ክፍያዎችን ለመፈጸም መንገድ ይፈጥራል፡፡ በዩጋዳ፣ ለምሳሌ፣ ጄኔራል፣ ሳሊም፣ ላይሀ፣ የቀድሞው ሽምቅ ተዋጊና የፕሬዝደንት ዩወሪ ሙሴቬኒ ግማሽ ወንድም፣ ከፓለቲካ ሙስና ጋር እጁ እንዳለበት በመጠቆሙ ከቦታው፣ የፕሬዝደንቱ፣ የመከላከያና ደህንነት የበላይ አማካሪ የነበረው እንዲነሳ ተደርጓል፡፡[42] የተበላሸ ምግብ ለዩጋንዳ ጦር ጀምሮ፣ አስተማማኝነት የሌላቸው ቲ -54 እና ቲ -55 ታንኮች፣ ሄሊኮፕተሮች፣ ሚግ -21 ተዋጊ ጀቶች እስከ መግዛት ደርሶዋል፡፡ ለዚህም፣ በከፍተኛ ቦታ ያሉ ወታደራዊ ባለስልጣናት የማያቋርጥ ህገ ወጥ ጉቦ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡[43] በ 2010፣ የካሜሮኑ የቀድሞ መከላከያ ረሚ ዘመካ፣ ከወታደራዊ ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ የገንዘብ ዝርፊያ እንዲታሰር ተደርጓል፡፡ ከ 2004 እስከ 2009፣ ስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ነው፡፡ በ 2013 የደቡብ አፍሪካው ፕሬዝደንት፣ ጃኮብ ዙማ፣ ወደ ሁዋላ እስከ 1999 at ድረስ፣ ከአርሚ እቃ ግዢ ጋር በተፈጸመ ሙስና ወደ ስድስት ቢሊዮን ዶላር መጥፋቱን የሚያሳይ ማስረጃ ለማቅረብ በሂደት ላይ ነው፡፡.

የተወሰኑ የአፍሪካ አገሮች በተቋሙ ውስጥ የመቆጣጠሪያ መንገድ ዘርግተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በአብዛኛው ፈረንሳይ ተናጋሪ የአፍሪካ ሃገሮች በመከላከያ ሚኒስቴር ተቋሞቻቸው የኢንስፔክሽን ክፍል አቋቁመዋል፡፡ ይህ ክፍል የመቆጣጠር፣ የማማከርና የጦር ሃይሉን የብቃት ደረጃ መፈተንና የመንግስት ፖሊሲ አፈጻጸሙን የመፈተን የስራ ድርሻ አለው፡፡ ከክፍሉ ዋና ዋና የስራ ተግዳሮቶች ውስጥ:

- የጦር ሃይሉን አስተዳደራዊና በጀታዊ እንቅስቃሴዎች ከህግና ደንብ ጋር መዛመዳቸውን ይቆጣጠራል፡፡
- በወታደራዊ መርሆዎች አነዳደፍና አፈጻጸም ላይ ይሳተፋል፡፡
- በየጊዜው ስለ መከላከያ ሃይሉ የሰው ሃይል አስተዳደር፣ መሳሪያ፣ ስልጠናና ሌሎች ፍላጎቶች ላይ ሪፓርት ያቀርባል፡፡

ምንም እንኳን የቁጥጥር ክፍሎች አስፈላጊ ተቋማዊ ፈጠራዎች ቢሆኑም ተገቢው ስልጣን ካልተሰጣቸው ውጤታማ አይሆኑም። የመከላከያ ሚኒስትርን ተቋም ሰንጠረዥ ለመቀመርና የቀድሞ ወታደራዊ መኮንኖችን የስራ ሃላፊነት ለመስጠት መሆን የለባቸውም። ኮንትራቶችና ውሳኔዎችን የሚቆጣጠረው ክፍል በተመሳሳይ ግለሰብ መፈጸሙ ከራስ ደህንነት ጋር የሚጋጭ ይሆናል። አንዳንዴም፣ ወዳጅነትና ለራስ የሚሰጥ ከፍተኛ ግምት በስራ ጣልቃ ይገባሉ። ይህም የቁጥጥሩን ስር ከወገናዊነት ከአድልዎ ውጪ ማድረግ ያስቸግራል። የስራው ጥራት ላይም ተጽእኖ ይኖረዋል።

በአፍሪካ የህግ አውጪው ክፍል በወታደራዊ በጀት ጉዳዮች ገብቶ ወታደራዊ መሪዎችን መጠየቅ ወይም በዝርዝር በጀት አፈጻጸም ራሱን ማስገባት የተለመደ አይደለም። በተለምዶ፣ የሃገር ደህንነት ይጎዳል ተብሎ ስለሚታመን፣ ፓርላም ወታደራዊ ወጪዎችን በበላይነት አይቆጣጠርም። ለምሳሌ፣ ኬኒያ ወታደራዊ በጀቱን በተመለከተ ከአፍሪካ ሰባተኛ ደረጃ ላይ ብትሆንም፣[44] በ 2012 ነው ህግ ያወጣችው፤ ወታደራዊ በጀት ሪፓርት ለፓርላማና ለፕሬዝደንቱ እንዲቀርብ የሚያዝ።

በሌሎች የአፍሪካ አገሮች፣ እንደ አንጎላ እና አልጄሪያ ያሉት፣ የፓርላማውን የበላይ ተቆጣጣሪነት ስልጣን የሚሰጥ ህግ ቢኖራቸውም፣ ተግባራዊ ሲደረግ አይታይም። በጋና፣ ከጸጥታና ወታደራዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ በፓርላማ ውስጥ ሶስት ኮሚቴዎች አሉ። እንዲሁም፣ የመከላከያና የአገር ውስጥ ጉዳይ ኮሚቴ በሊቀ መንበርነት የሚመራው በትልቁ ተቃዋሚ ፓርቲ ነው። ይህም፣ የጸጥታ በጀትን አፈጻጸም በተመለከተ የመቆጣጠሪያ እድል ፈጥሮዋል። አሁንም ቢሆን፣ የበጀት ጉዳይ ሲነሳ፣ የብሄራዊ ደህንነት እንደምክኒያት ስለሚቀርብ የሚጋፈጥ ሃይል አይኖርም።[45] በቶጎ 25 % የአገሪቱ በጀት ለወታደሩ ቢውልም፣ ከሌሎች በጀት ትልቁ ቢሆንም፣ በጣም ያነሰ ቁጥጥር ነው ያለበት።[46] በሌሎች አገሮች፣ እንደ ናይጄሪያ ያሉት፣ ማእከላዊነት ያለው አሰራር አይከተሉም። በዚህም ባህር ሃይል፣ አየር ሃይልና ምድር ጦሩ የየግላቸውን በጀቱ የማየት ስልጣን አላቸው።[47] ይህ አሰራር ለቁጥጥር አመቺ ያልሆነና ለብክነት የሚያጋልጥ ነው።

በተጻራሪው፣ እንደ ሴኔጋልና ደቡብ አፍሪካ ያሉት አገሮች ውጤታማ የሆነ የሲቪል አስተዳደር ስልጣን በመከላከያ መስሪያ ቤቶቻቸው ውስጥ ፈጥረዋል። ይህም በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ የሆነ የበጀ ቁጥጥር

ፈጥረዋል፡፡[48] በቡርኪና ፋሶ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ዩጋንዳ፣ በመረቀቅ ላይ ያለ፣ የመከላከያ በጀትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ህግ አለ፡፡ እንደ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካና ዩጋንዳ ባሉ አገሮች የፓለቲካ ጣልቃ ገብነት ሲፈጸም ጠንካራ የሆነ የሲቪል ማህበረሰብ ድምጽ መንግስትን ተጠያቂ ያደርጋል፡፡ በ ለምሳሌ፣ የደቡብ አፍሪካ መከላከያ ሚኒስቴር፣ ሊንዲወ ሲሱሉ፣ በህዝብ ተቃውሞ ከስልጣን ተነስታለች፤ ለፕሬዝደንት ዙማና ለምክትሉ ምትላቴ፣ የግል መጠቀሚያ አውሮፕላን በ $200 ሚልዮን ለመግዛት ምስጢራዊ ድርድር ማድረጓ ነገር የህዝብ ቁጣ መነሻው ሆኖዋል፡፡

**ደካማ የሆነ እሴት አጠቃቀም የስራ አፈጻጸም ችሎታን ያዳክማል፡፡** ብቃት ያለው አስተዳደር ለወታደሩ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ጠንካራ አስተዳደራዊ ተግዳሮት ብቻ ነው፡፡ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የአፍሪካን ሰራዊቶች በጀታቸውን በውጤታማ ሁኔታ እንዲቆጣጠሩ የሚረዳቸው የዚህ ችሎታ አለመኖር በሁሉም ደረጃ በአፍሪካ ሰራዊት ውስጥ የሚታይ ነው፡፡

ዘርና ፓለቲካን ያማከለ ስልጣን እድገት አሰጣጥ፣ በአንዳንድ አገሮች የስልጣን ተዋረድን ያዛባ ነው፡፡ ከ 2012 ቀውስ በፊት፣ የማሊ አርሚ 50 ጀነራሎች ነበረው፡፡ ለ 20,000 ወታደሮች፣ አንድ ጀነራል ለ 400 ወታደር ነበራት፡፡ ኒጀር ደግሞ ከ 600 ወታደሮች ያሉት፣[49] በተለምዶ በአንድ ብርጋዴር ጄኔራል በንጽጽር፣ አንድ የኔቶ ብርጌድ፣ ወይም በሙሉ ጀነራል ነው የሚታዘዘው 3,200-5,500 ወታደሮች ያሉት ነው፡፡ ይህ ሚዛኑን ያልጠበቀ ያለቃና ጭፍራ ስብጥር በአፍሪካ የተለመደ ችግር ነው፡፡ ሁልጊዜም፣ የመኮንኖች ቁጥር መብዛት ከወታደር ቁጥር ጋር ሲነጻጸር፣ ሰራዊቱን ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ የመኮንኖች ቁጥር ግሽበት ለእዝ ድክመት ከመጋበዙም በላይ ተጨማሪ የበጀት ጫና ይፈጥራል፡፡ ለስነ ስርኣት መጓደልም ምንጭ ነው፡፡ ከፍተኛ መኮንኖች፣ ፖለቲካዊ ሹመት ለማይገባቸው መኮንኖች ተሰጥቶዋል የሚል ስሜት ሲፈጠርባቸው፣ ለአዳዲሶቹ ተሹዋሚ ጀነራልና ኮሎኔል መኮንኖች አይታዘዙም፡፡ ይህም ስርኣተ አልበኝነት በወታደሩ ውስጥ ይፈጥራል፡፡ ይሄም የእዝ ሰንሰለቱን ያበላሻል፡፡ ለምሳሌ፣ የዩጋንዳ ፕሬዝደንት ሙሴቪኒ፣ ልጃቸው ብርጋዴር ጄኔራል ሙሃዚ ኬያንሩጋባ፣ ከ 15 አመታት ግልጋሎት በሁዋላ፣ የልዩ ሃይል አዛዥ መሆን የፖለቲካ ጨዋታ እንቆቅልሹን አሳድጓል፡፡[50]

የተበላሸ ተሽከርካሪዎችና የጥገና እጥረት ለአፍሪካ የመከላከያ ሃይል መሽመድመድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። አየር ሃይል በአፍሪካ እየተመናመነ ነው። የውጪ አጋሮች ትብብር ማቆምና የበጀት ቅነሳ ብዙ አውሮፕላኖችን በቆሙበት እንዲቀሩ አድርጓል። በርካታ ፓይለቱም አርሚውን ጥለው እንዲሄዱ አድርጓል። እድለኛ የሆኑት ወደ ግሉ አየር ትራንስፖርት ገብተው የግለሰቦች ተቀጣሪ ሆነዋል። በተመሳሳይም፣ ደቡብ አፍሪካ ብቻ ናት ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ የባህር ሃይል ያላት ይህ በመሰረቱ መጥፎ ነገር አይደለም። ምክኒያቱም ተቀዳሚ ተጠቃሽነት ያለው የባህር ላይ አደጋ ባብዛኛው የሚፈጸመው ጠረፍ አጠገብ ያለና በኢኮኖሚክ ዞን ውስጥ 200 ናውቲናቲካል ማይልስ ክልል ውስጥ ስለሆነ ቢሆንም[51] ቅሉ ትንንሽ ባህር ሃይል ያላቸው እንደ ካሜሮን፣ ኮት ዲቩዋር፣ ጋቦን፣ ኬኒያ፣ ሴኔጋል፣ እና ታንዛኒያ በጥገናና ዘመን ባለፈበት መሳሪያ ይሰቃያሉ።[52]

ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገሮች ውስጥ ያሉ አርሚዎች የብቃት ማሽቆልቆል የተከሰተው፣ በ 1990 ዎቹ ቀዝቃዛው ጦርነት ሲያበቃ ነው። ከዛ በፊት የነበሩት ሙያዊ ብቃት ባይኖራቸውም፣ ሊታደስ የሚችል፣ ቢያንስ መሳሪያ ነበራቸው። እነዚህ መሳሪያዎች የተሰጡትም ሆነ የሚታደሱት በሃያላን መንግስታቱ መካከል ያለውን ፍጥጫ ለማስቀጠል ነበር። የቀዝቃዛው ጦርነት በድንገት ማለቅ ይሄንን ምንጭ አደረቀው። ከምስራቁም ሆነ ከምእራቡ ያለው ድጋፍ ሲቆም፣ ከሰሃራ በታች ያሉ ሃገሮች አርሚ የስራ ብቃቱን በትንሹም ቢሆን ማስቀጠል አልቻለም። ለምሳሌ፣ በቡርኪና ፋሶ፣ በ 1999 የምህንድስና እዙን ያግዘ የነበረው የጀርመን እርዳታ ቆመ። በዚህም የተነሳ ይህ ክፍል በቡርኪና ፋሶ ገጠር መንገዶች ጥገና ላይ የነበረው ስራ እንዲቆም ተገደደ።

በ 2012-2013 በማሊ የተነሳው ረብሻ በጎረቤት አገሮች ሰራዊት ውስጥ ያለውን የማኔጅመንት ችግር አሳይቶዋል። ምንም እንኳን ያለፈ ሰላም ማስከበር ልምድ ቢኖረውም፣ ኢኮዋስ፣ አስተማማኝ የሆነ ሃይል መድቦ በፍጥነት እየተንቀሳቀሰ የነበረውን የጂሃዲስት ሃይል ማስቆም አልቻለም። የኢኮዋስ ማመንታት በመመልከት፣ በተባበሩት መንግስታት ሬዞሉሽን 2085 መሰረት፣ የማሊን የግዛት ሉአላዊነት ለማስከበር፣ ፈረንሳይ፣ ጣልቃ ገብ ጦር ላከች። ከተልእኮዋ ውስጥም፣ የጂሃዲስቶችን መሰረታዊ ቤዝ ማሳጣትንም ይጨምራል። እውነታውን ግን፣ ከጥቂት የምእራብ አፍሪካ ሃገሮች በስተቀር፣ በራሳቸው አቅም ጦር ከቦታ ቦታ ማነቃነቅ

የሚችሉ የሉም።

ሁሉም የአፍሪካ ሰራዊት ሁዋላ ቀሮች አይደሉም። ሞሮኮ፣ አልጄሪያ እና ደቡብ አፍሪካ በአጠቃላይ ሲታይ በደንብ የሰለጠነና ውጤታማ የሆነ፣ የጥምር ጦር ውጊያ ማካሄድ የሚችል ጦር ሃይል አላቸው። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጦር በሶማሊያ ምስጋና ሊቸረው ይገባል። ከዩጋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ጅቡቲ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬኒያና ሴራ ሊዮን የተውጣጣ ጦር በርካታ የሶማሊያ ከተሞችን ለማረጋጋትን ስርዓት ለማስፈን ረድቶዋል።[53] በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የአክራሪ እስላም ሃይሎችን እንቅስቃሴ ለመግታት በአድራር እፎግሃስ፣ በሰሜን ማሊ፣ በ 2012 ህብረ ብሄሩን ጦር በ ማገዝ የቻድ ጦር ሃይል ወደ 2,000 የሚጠጋ የበረሃ ውጊያ ልምድ ያላቸው ወታደሮች ማሰማራት ችሎዋል። የናይጄሪያ የጦር ሃይል ሰሜን ማሊን ለማረጋጋት ወሳኝ ሚና ተጫውቶዋል። ከደቡብ አፍሪካ፣ ታንዛኒያ፣ ማላዊ የተውጣጣ ወደ 3,000 የሚጠጋው የተባበሩት ጣልቃ ገብ ጦር፣ በዲሞክትራቲክ ኮንጎ፣ በ 2013 ፣ የኤም 23 ተዋጊ ሃይሎችን ለማሸነፍ ወሳኝ ሚና ተጫውቶዋል።

**የሞራል ማነስ** የአፍሪካ ሰራዊት፣ ብቃት ያላቸው፣ በአለም ታዋቂ ወታደራዊ ኮሌጆች የሰለጠኑ መኮንኖች አፍርቶዋል። እንዳለመታደል፣ እነዚህ መኮንኖች ብቃትና ከፍተኛ ሙያዊ ክህሎት በማእረግ እድገትና ሽልማት በማይወስዱበት ቦታ የሚጠበቅባቸውን ፍሬ ማፍራት አልቻሉም። የዚህም ውጤት የሆነው፣ ያለ ስራ መቀመጥና የክህሎቶች መሸርሸር፣ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ መኮንንም ፍላጎት የሚያጠፉ ነው። ለቀጣዩ የወታደሮች አመጽ መሰረት ጣይ ሁኔታን ይፈጥራል። አላማ የለሽነትና በመሪዎቻቸው የተተው ስለሚመስላቸው።

የሞራል ጥንካሬ በጦር ሜዳ አስፈላጊ ነው። ሞራል ከሌለ ሽንፈት የማይቀር ነው። የማሊ ወታደሮች ሞራል ማጣት፣ ከአክራሪ እስላሚስቶችና ከቱአሬግ ተገንጣዮች ጋር በተካሄደው የ 2012-2013 ውጊያ፣ በርካታ ምክኒያቶች አሉ። ከፓለቲካ አለመረጋጋት በተጨማሪ፣ የከፍተኛ መኮንኖች ሙስናና በቂ ድጋፍ ግንባር ላሉት ወታደሮች አለመደረጉ ጥቂቶች ናቸው።

ሙስና በከፍተኛ መኮንኖች ሲፈጸም የጦሩን ሞራል የመግደል አቅሙ ከፍተኛ ነው። በቀጣይም ሙስናን የመታገስ ችሎታቸውና እራሳቸውም በሙስና የመሳተፍ እድላቸው ከፍ ይላል።[54] ክፍያው በጣም አነስተኛና ጊዜ ጠብቆ በማይከፈልባቸው አገሮች፣ ወታደሮች ከአካባቢያዊ ነዋሪዎች አስገድደው መውሰድ ይገደዳሉ። ወይንም ወደ ሌላ ትርፍ ወደሚያመጡ

እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ይገደዳሉ፡፡ እንደ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች፣ የማሊ ወታደራዊ መኮንኖች ከተመለመለው የወታደር ቁጥር በላይ ሪፓርት በማድረግ ትርፉን ገንዘብ ወደ ኪሳቸው ያስገባሉ፡፡ መሳሪያውንም በመሸጥ ለራሳቸው ገቢ ያደርጋሉ፡፡[55] አንዳንድ ጊዜ ወታደሮች ወደ አድማ ይወጣሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ኮንጎ፣ በምስራቁ የአገሪቱ ግዛት ለተመደቡት ወታደሮች አለመከፈል፣ የሚዲያ ሪፓርት እንደገለጸው ከከፍተኛ መኮንኖች ሙስና ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአጸፋው፣ ወታደሮች የአካባቢያዊውን ህዝብ ከሎርድ ሬዚስታንስ አርሚ ጥቃት መከላከል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡[56]

በጣም ሃላፊነት የጎደላቸው ወታደሮች ወደ ተደራጀ ወንጀል ፍጹም ገብተዋል፡፡ ከ 1990 ው የደሞዝ አለመከፈል ተከትሎ፣ የጊኒ ቢሳው ከፍተኛ ወታደራዊ አመራሮች የጦር መሳሪያዎች፣ የሚቀበሩ ፈንጂዎች ለካማንስ ተዋጊዎች መሸጥ ጀመሩ፡፡ በመጨረሻም፣ ወደ አደገኛ ዕጽ ንግድ ተሻገሩ፡፡ ጊኒ ቢሳውን ሲያምስ የቆየው፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ አመጽና የመንግስት በሙስና መዘፈቅ በቀጥታ ከአደገኛ እጽ ንግድ ጋር የተያያዘ ነው፡፡[57]

ይሄው የአደገኛ ዕጽ ንግድ ካርቴል ሌሎችንም የምእራብ አፍሪካ ሀገሮች አዳርስዋል፤ ወታደራዊና ፖለቲካዊ መሪዎቻቸውን በተለየ ተጽእኖ ስር እንዲወድቁ አድርጓል፡፡ የቀድሞው የማሊ መሪ፣ አማዱ ቱማኒ ቱሬ፣ በሰሜኑ ክፍል ተጽእኖ ለመፍጠር፣ የተደራጀ የወንጀል ድርጅት እንደ መሳሪያ ተጠቅሞዋል፡፡[58] የማሊ ወታደራዊ ክፍል አባላቶች፣ ለወንጀለኛ እጽ አስራጊ ወንጀለኞች ጊዜያዊ እርዳታ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡[59] አንዳንድ ጊዜ፣ የማሊ ባለስልጣን በሁለት ወንጀለኛ ክፍተት መካከል በሚደረግ ግጭት ተሳትፈው ተገኝተዋል፡፡[60] ምንም እንኳን በቂ ምክኒያትም ባይሆንም፣ በዲሞክራሲ የተመረጠ መሪ ማውረድ የማሊን መንግስት ተአማኒነትንና ህጋዊነት አሳጥቶታል፡፡ ውጤታማነቱንም ሸርሽሮታል፡፡

**ያልተማከለ ወይም ጊዜው ያለፈበት ተልእኮ** የስራ አፈጻጸም ስታኒስላቭ አንድሬዜውስኪ እንዳመለከተው፣ በጉዳይ ያልተጠመደ ሰራዊት፣ የውጪ አደጋ በሌለበት ሁኔታ፣ በአገር ውስጥ ጣልቃ የመግባት እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡[61] ይህ ሁኔታ፣ በአፍሪካ ውስጥ እውነታነት አለው፡፡ ብዙ የአፍሪካ ሚሊታሪዎች ራእይና ግልጽ የሆነ አላማ የላቸውም፡፡ ይሄንን ስናይ፣ ሁዋላ ቀር ተሽከርካሪዎች፣ ያልሰለጠነና ሞራል የሌላቸው ወታደሮች የትልቁ ፈተና ምልክቶች ናቸው፡፡ በቁጥር የተወሰነ የአፍሪካ አገሮች ብቻ

ናቸው፡፡ በግልጽ የተቀመጠ የብሄራዊ ደህንነት መርሆ ያላቸው፡፡ የደህንነት መርሆ፣ ያለህን አቅም፣ ማስቀደም ካለብህ ፍላጎት ጋር ለማጣመር፣ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም በተቋሞች መካከል መቀናጀት ለመፍጠር፣ በተለያዩ የመንግስት ቅርንጫፎች መካከል የጋራ የሆነ መግባባት በመፍጠር መንግስትን፣ አርሚውንና የሲቪል ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡

ለብዙ የአፍሪካ አገሮች መከላከያ ሃይሎች፣ የአርሚ መሰረታዊ መመሪያ መሰረት ያደረገው አገርን ከውጪ ጠላት መከላከል ነው፡፡ ሆኖም ግን፣ በአገሮች መካከል የተደረጉ ግጭቶች በጣም ውስን ናቸው፡፡ ከዚህም፣ በተጨማሪ የአፍሪካ ሀገሮች በመካከለኛው የሚነሱ ግጭቶትን ለማስወገድ አለም አቀፋዊ ህጋቶችን ተጠቅመዋል፡፡ የወሰን ግጭቶች፣ በናይጄሪያና በካሜሮን መካከል፣ በቡርኪና ፋሶና በማሊ፣ እንዲሁም በቤኒንና በኒጀር መካከል በተነሱ ጊዜ ሄግ በሚገኘው አለም አቀፍ ፍርድ ቤት አማካኝነት እንዲፈቱ ተደርጓል፡፡

በአንጻሩ፣ የአፍሪካ አደጋ በአብዛኛው የሚመነጨው ከውስጥ ነው፡፡ ቦኮ ሃራምና የኒጀር ዴልታን ነጻ ለማውጣት የሚታገለው እንቅስቃሴ ለዘመናት የናይጄሪያን ባለስልጣናት ሲፈታተን ቆይቶዋል፡፡ የአንጎላ እና የሴኔጋል መንግስታት ለአስርተ አመታት ተገንጣይ ሃይሎችን በካቢንዳና ካሳንማል ግዛቶች ሲዋሁ ቆይተዋል፡፡ የቱአሬግ ገንጣዮች በእስላም አክራሪዎች በመደገፍና በባማኮ የነበረውን የፓለቲካ አለመረጋጋት በመጠቀም የሰሜን ማሊን ለመቆጣጠር ችሎዋል፡፡ የዩጋንዳው ጆሴፍ ኮኒያርድ በሚሊሺያው በመደገፍ በዩጋንዳ፣ በኮንጎ፣ በመሃከለኛው አፍሪካ ህዝብ ላይ አሰቃቂ ግፍ ፈጽሞዋል፡፡ አደገኛ የሆነው አል ሸባብ ለሶማሊያ አለመረጋጋት ከፍተኛ አደጋ ሆኖ ቆይቶዋል፡፡

እነዚህ አገር በቀል እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩት ነገር ቢኖር በወታደራዊ ግዳጅ አፈጻጸምና በእውነተኛ የጸጥታ ችግር መካከል ያለውን ልዩነት ነው፡፡ በአንዳንድ አገሮች፣ መደበኛ ሰራዊቱን የሚጋፈጡት የተሻለ ትጥቅ በተሻለ ሁኔታ መነቃነቅ የሚችሉና ስለአካባቢው የተሻለ እውቀት ያላቸው ናቸው፡፡[62] በዚህም የተነሳ የአፍሪካ የደህንነት ሃይል የተሻለ ስልጠናና ሙያዊ ክህሎት ያለው መሆን አለበት፡፡ የአፍሪካ መሪዎች ይህንን ሁኔታ ተረድተው፣ ለጸጥታ ተቋሞቻቸው ግልጽ የሆነ መርሆ እስካላወጡና ከወደፊት የረዥም ጊዜ አላማ ጋር ካልቀራፁ፣ ጦራቸውንና ያላቸውን አቅም ለተጋረጠባቸው የጸጥታ ደህንነት ማዘጋጀት ይቸገራሉ፡፡

# የአፍሪካን ወታደሮች ክህሎቶች ለመገንባት ቅድሚያ ነገሮች

በማይታለፉ በሚመስሉ ብዙ ችግሮች፣ የ አፍሪካ ወታደሮች ሙያዊ ክህሎቶች የሩቅ ህልም ሊመስሉ ይችላሉ። ነገር ግን ተስፋ አለ። መሻሻል ለማምጣት በሶስት ሁሉን አቀፍ ቦታዎች ላይ ማሻሻያዎችን ማሳለፍ ይጠይቃል፡ የወታደሩን አላማ መከለስ፤ ወታደሮች የሚሰሩበትን ሁኔታ ከፖለቲካ ነጻ ማድረግ፤ ሞራልን እና ተጠያቂነትን በወታደር ባህል ውስጥ ተቋምአዊ ማድረግ

## የወታደሩን አላማ መከለስ

ወታደሮች ውድ ናቸው። ክህሎት ያለው ወታደር የተማረ፣ የሰለጠነ፣ የታጠቀ፣ እና የተጠገነ መሆን አለበት። ስለዚህ ከወታደር ምን እንደሚጠበቅ ማወቅ ያስፈልጋል፤ ይህም ንብረቶች እንዳይወድሙ ይረዳል። በአብዛኛው የአፍሪካ ወታደሮች የተቀረጹት እና የተደራጁት የውጭ ወራሪ ሃይልን ለመመከት ሲሆን ላልተለመዱ የደህንነት ስጋቶች እንደ ውስጣዊ ግጭቶች፣ ሃገር ዘለል ወንጀሎች፣ የባህር ላይ ዝርፊያ፣ አሸባሪነት፣ እና የትንንሽ መሳሪያዎች መንሰራፋት የመሰሉትን በአግባቡ መጋፈጥ አይችሉም። ይህ አለመጣመር በአፍሪካ ወታደሮች ያለመብቃት ቁልፉ ምክኒያት ነው። በተጨማሪም፣ ወታደሮች ለፖሊሳዊ ስራዎች ማለትም ከወታደራዊ ጦርነት በጣም ለተለየ ተግባር ይላካሉ። ይህ ራሱ ለከፋ የሰብአዊ መብቶች ሪኮር እና ለፕሮፌሽናሊዝም አለመሆን ያደርጋቸዋል። ለአገሮች ነባራዊ ስጋቶች ለመመከት እንዲሁም የወታደሮቻቸውን ክህሎቶች ለማሻሻል፣ የአፍሪካ መንግስታት የደህንነት ሴክተሩን የሚያዩበት መንገድ መቀየር አለባቸው። የደህንነት ሃይል መዋቅሩን ማደረጃጀት ለተለዩት ስጋቶች በተሻለ የሚመጥን እና እነዚሁን አላማዎች ወደ ሁሉን አቀፍ እና የተማከለ የመከላከያ ፖሊሲ መፍጠር የአፍሪካን ወታደሮች የስራ ብቃት እና ክብር ያሳድጋል።

## አላማውን እንደገና መወሰን፤

ወታደሮች ውድ ናቸው። ክህሎት ያለው ወታደር የተማረ፣ የሰለጠነ፣ የታጠቀ፣ እና የተጠገነ መሆን አለበት። ስለዚህ ከወታደር ምን እንደሚጠበቅ

ማወቅ ያስፈልጋል፤ ይህም ንብረቶች እንዳይወድሙ ይረዳል። በአብዛኛው የአፍሪካ ወታደሮች የተቀረጹት እና የተደራጁት የውጭ ወራሪ ሃይልን ለመመከት ሲሆን ላልተለመዱ የደህንነት ስጋቶች እንደ ውስጣዊ ግጭቶች፣ ሃገር ዘለል ወንጀሎች፣ የባህር ላይ ዝርፊያ፣ አሸባሪነት፣ እና የትንንሽ መሳሪያዎች መንሰራፋት የመሰሉትን በአግባቡ መጋፈጥ አይችሉም። ይህ አለመጣመር በአፍሪካ ወታደሮች ያለመብቃት ቁልፉ ምክኒያት ነው። በተጨማሪም፣ ወታደሮች ለፓሊሳዊ ስራዎች ማለትም ከወታደራዊ ጦርነት በጣም ለተለየ ተግባር ይላካሉ። ይህ ራሱ ለከፋ የሰብአዊ መብቶች ሪኮር እና ለፕሮፌሽናሊዝም አለመሆን ያደርጋቸዋል። ለአገሮች ነባራዊ ስጋቶች ለመመከት እንዲሁም የወታደሮቻቸውን ክህሎቶች ለማሻሻል፣ የአፍሪካ መንግስታት የደህንነት ሴክተሩን የሚያዩበት መንገድ መቀየር አለባቸው። የደህንነት ሃይል መዋቅሩን ማደረጃጀት ለተለዩት ስጋቶች በተሻለ የሚመጥን እና እነዚሁን አላማዎች ወደ ሁሉን አቀፍ እና የተማከለ የመከላከያ ፖሊሲ መፍጠር የአፍሪካን ወታደሮች የስራ ብቃት እና ክብር ያሳድጋል።

**አላማውን እንደገና መወሰን፤** የአንድ አገር መከላከያ ፖሊሲ አላማ ማካተት ያለበት ኢፖለቲካዊ፣ ተጠያቂ፣ የሚችል፣ እና ብዙ የማያስከፍል ወታደርን ነው።[63] አንድ ወታደር በተራው አላማውን እንዲመታ ተደርጎ መቀረጽ አለበት። ለትልቁ ወደ ውጭ የሚያይ ወታደር አስፈላጊነት ከሌለ፣ መንግስታት የታጠቀ ሃይላቸውን ብቃት ያለው እና ለነባራዊ የአገሪቱዋ የደህንነት ስጋቶች የሚሰራ እንዲሆን ማስተካከል አለባቸው።[64] የዚህ ሂደት ቁልፍ አካል የውጭ እና የውስጥ ስጋቶችን የሚያማክል የብሄራዊ የደህንነት ስትራቴጂዎችን ማጎልበት ነው።

የአፍሪካ መንግስታት ከሚያጋጥማቸው ችግሮች አንዱ ጦርነት በሌለበት ጊዜ ወታደሮቻቸውን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነው። የጋና የታጠቀ ሃይል (ጂኤኤፍ)፣ እንደ አብዛኛው የአፍሪካ ወታደሮች፣ ለብዙ አመታት ሃገሪቱዋን ከውጭ ወራሪ መጠበቅ ኖሮባቸው አያውቅም። ክህሎታቸውን ለመጠቀም እና ለማዳበር፣ ጂኤኤፍ የአገር ውስጥ የደህንነት ተቋማትን እንዳስፈላጊነቱ ደግፎዋል፤ እንዲሁም በተለያዩ አለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ስራዎች ላይ ተሳትፎዋል። ጂኤኤፍ በደንብ የተደራጀ እና ድጋፍ ለመስጠት የተዘጋጀ፤ ከመጓጓዣ እና ግንኙነቶች እስከ ህግና ስርኣት ማስከበር፤ በተለያዩ የአገራዊ ውድመቶች

ጊዜ ተሳትፎዋል፡፡ በህክምና ሰራተኞች እና የወታደራዊ ሆስፒታሎች፣ ለጋናውያን እንክብካቤ ሲያቀርብ፣ መንግስትንም በበሽታ ማጥፋት እና የጤና ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ አግዞዋል፡፡ ጂኤኤፍ ፖሊስን ህግ በማስፈን ሲረዳ በተለይ በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ግጭቶች አረመረጋጋትን ሲፈጥሩ የተቀናጀ የወታደር ፖሊስ ቡድኖች በከተማ ውስጥ ያሉ በመሳሪያ የተደገፉ ዝርፊያዎችን እና ሌሎች ወንጀሎችን ይመክታሉ፡፡[65] ጂኤኤፍ በተጨማሪም የመሬቶች እና የተፈጥሮ ሃብቶች ሚኒስቴርን የደን ሃብቶችን እና ፓርኮችን ከህገወጥ መንጣሪዎች ለመጠበቅ ያግዛል፡፡[66]

ሴኔጋልም ወታደሮቸዋን በአንዳንድ የህዝብ ስራ ፕሮጀክቶች በታወቀው የሲቪል ወታደር ትብብር አርሚ ኔሽን ተብሎ በሚጠራው ላይ ታሳትፋለች፡፡ በአርሚ ኔሽን፣ የሴኔጋል የታጠቁ ሃይሎች የመሰረተ ልማት፣ ብሄራዊ አገልግሎት፣ እና የአካባቢ ጥበቃን ያግዛሉ፡፡ ከሲቪል ማህበረሰቡ ጋር በመስራት ህይወታቸውን ማሻሻል እንዲሁም ኢፖለቲካዊ እና ክህሎት ያለው ሆኖ መቆየት እራሱን የሚደግግም የመልካም ስራ፣ ክብር፣ እምነት፣ እና ኩራት በሴኔጋል ህዝብ እና በወታደሩ መሃል ፈጥሮዋል፡፡[67]

ምንም እንኳን በአካባቢው ማህበረሰቦች ግንኙነት መፍጠር የሚፈለግ ቢሆንም፣ ወታደሩ ማተኮር ያለበት በተነጻጻሪ ብቃት ባለው ቦታዎች ላይ ነው፡፡ በወታደሩ የሚሰሩ የግንባታ ፕሮጀክቶች፣ ለምሳሌ፣ በበለጠ ውድ ሲሆኑ፣ የግል ሴክተር የኢኮኖሚ እድገቱን ያቀዘቅዛሉ፡፡ በተጨማሪም፣ በአብዛኛው የአፍሪካ አገሮች አደገኛ የደህንነት ስጋት ሲኖርባቸው፣ ይህም በተፈጥሮአቸው ሃገር ዘለል የሆኑትንም ይጨምራል፡፡ ውስን የሃብት መኖር ምክኒያት፣ የደህንነት ሴክተሩ ትኩረት እነዚህን ስጋቶች ላይ በመስራት መሆን አለበት፡፡

የሚፎካከሩትን ቅድሚያ ተግባሮች በማየት፣ የፓሊሲው ወሳኝነት አስፈላጊ ነው፡፡ ፍለጋ እና ማዳን፣ የአደንዛዥ እጽ ዝውውር፣ እና የባህር ላይ ዘረፋ ወታደሩ ብቃቱን ማዋል የሚችልባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ስጋቶች ላይ መስራት ያለበት ግን ከሌሎች የደህንነት ሴክተር ተዋናዮች እና የመንግስት ወኪሎች ጋር በጥንቃቄ በማስተባበር መሆን አለበት፡፡[68] በተመሳሳይ፣ በብዙ ሁኔታዎች የወታደሩ መሪዎች የአገር ውስጥ አሸባሪነትን በመዋጋት ከደጋፊ ሚና የዘለለ መጫወት የለባቸውም፡፡ ፖሊስ፣ ስለላ፣ እና ፓራ ወታደር ድርጅቶች ለንደነዚህ አይነት ስጋቶች የሚሆን ያተኮረ መልስ ለመስጠት የተሻለ የሰለጠኑ ናቸው፡፡[69]

እንዲሁም፣ በአብዛኛው የአፍሪካ ወታደሮች በአለም አቀፍ ሰላም ማስከበር ስራዎች ላይ የመሳተፍን ጥቅሞች አይተዋል፡፡ እነዚህ ስራዎች የሚያካትቱት አጠቃላይ የደህንነት ችግሮች በአህጉሪቱ ላይ ሲሆን፣ ድንበር ዘለል ችግሮች እና ተያያዥ የደህንነት ስጋቶችን ነው፡፡ በተጨማሪም የሰራዊቱን ብቃት፣ አላማ፣ እና ኩራት ይገነባሉ፡፡

**የወታደር እድገትን መደገፍ፤** የአሁኑ የተበላሸ አለመጠገን፣ የአስፈላጊ መሳሪያ አለመኖር፣ እና የአየር እና የባህር ሃይሎች ችሎታ ማነስ ለብዙ የአፍሪካ ወታደሮች የመሻሻል እድል ይፈጥራሉ፡፡ የማንኛውም የደህንነት ሃይል አላማ የደህንነት ስጋቶች እንዳይነሱ መከላከል፣ ከተነሱም በበቂ መልኩ መልስ ለመስጠት ነው፡፡[70] ይህንን አላማ ለማሳካት የግዴታ ተጨማሪ ታንኮች፣ ጀቶች፣ እና መርከቦች አያስፈልጉም፡፡ በአብዛኛው ስራዎች የማስተካከል ወይም የመልሶ ማጥቃት አይነት ተፈጥሮ ያላቸው ሲሆኑ፣ የወታደሩ አላማ ዜጎቹን መከላከል እና መጠበቅ መሆን አለበት፡፡ ይህንን ለማድረግ፣ የወታደሩን የሰው ሃይል ማጠናከር ተቀዳሚ ቦታ ሊሰጠው ይገባል፤፤ ይህም የበቁ፣ የሚጠበቡ፣ እና የተከበሩ ግለሰቦችን እና ቡድኖችን ማሳደግ ይጨምራል፡፡ የማስተካከል ስራዎች በየማህበረሰቡ ውስጥ መኖራቸው እንዲቀጥል፣ ስለዚህም የሚጠብቁት ማህበረሰብ አባል የሆኑ ወታደር አባሎችንም ማካተት አለበት፡፡ በወታደሩ እና በማህበረሰቡ መሃከል የአካባቢውን ትርጉም ለመረዳት እና ክብር እና እምነት ለመገንባት ከዚህ የበለጠ መንገድ የለም፡፡ እናም የበጀት ቅነሳዎች ሲኖሩ፣ ዘመናዊ እና ብዙ ወጪ የማይጠይቁ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍ እና ብልህ በሆኑ የመዋጊያ ስትራቴጂዎች፤፤ ችሎታቸውን በማህበረሰቡ ካላቸው ጥልቅ እውቀት ጋር በማጣመር የደህንነት ስጋቶችን መከላከል አለባቸው፡፡

የአፍሪካ ወታደሮች ማተኮር ያለባቸው ከብዛት ይልቅ ምን አይነት ወታደር እንደሚፈልጉ ነው፡፡ ይህ ወደ ወታደሩ ሞራል ብቃት ይመራናል፡፡ ወታደርነት ተራ ሙያ አይደለም፡፡ ከፍ ያለ ታማኝነት፣ ችሎታ፣ ጽናት፣ እና መስዋትነት ይጠይቃል፡፡ የአፍሪካን የታጠቁ ሃይሎች ክህሎት ለመጨመር ሂደት አካል የሚጠይቀው ትናንሽ ነገር ግን የተሻለ የሰለጠኑ እና የታጠቁ ሃይሎችን ነው፡፡ ይህም ኩራትን ወደ መገንባት እና ወደ ላቀ ሙያዊ ክህሎት ሲያግዝ የተቀጣሪዎችንም ችሎታ ይጨምራል፡፡

## የክቡር ዘበኞዎችን ማሻሻል

የትላልቅ ባለስልጣናት እና የፖለቲካ ተቋማት ጥበቃ ለመንግስት ቀጣይነት እና ደህንነት ወሳኝ ነው። ሆኖም፣ በአብዛኛው የክቡር ዘበኞዎች በአፍሪካ የሚሆኑት ተለቅ ያሉ የወታደር ክፍሎች ከተነጻጻሪ የላቀ መሳሪያ እና ረዘም ያሉ ስራዎችን የመስራት አቅም ያለው ነው። ፕሬዝደንቶች እና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት የሚፈልጉት ምስጢሩ የተጠበቀ ሃይል ሆኖ አጣዳፊ ስጋቶችን መመከት የሚችል ነው። ማንኛውም የተራዘመ ስጋት በፖሊስ፣ ገንዳመሪ፣ ወታደር፣ ወይም ሌላ የደህንነት ኤጀንሲ ስር መሰራት አለበት።

ክቡር ዘበኛ የሪፐብሊኩን አላማ በመያዝ የተወሰነ ጎሳ ላይ የተመሰረተ የሰራዊት ክፍል የተወሰነ መንግስትን ለመጠበቅ መወሰን የለበትም። ቢቻል፣ ብሄራዊ ወገንተኛነትን ለማረጋገጥ፣ የክቡር ዘበኛ መዋቀር ያለበት በወታደር ኦፊሰሮች፣ ፖሊስ ኦፊሰሮች፣ እና ገንዳርመስ፣ እና ስብጥሩም የሁሉንም ማህበረሰብ መወከል አለበት። እነዚህ ትንሽ፣ የተቀናጁ ክፍሎች ልዩ ስልጠና ሲቀበሉ፣ አቅማቸውን እና ሙያዊ ኩራታቸውን በሂደቱ ይገነባል። ይህ አካሄድ ከተሰራበት በሁዋላ፣ ከፕራቶሪያን ጠባቂዎች ጥሰቶች እንደመከላከያ ሆኖ ያገለግላል። ከበቂ ሰራተኛ በላይ ባለው እና ብዙ ክፍያ በሚከተለው ክቡር ዘበኛ ላይ ቅነሳ ማድረግ ሃብትን ለማዳን እንዲሁም የአገሪቱን የደህንነት ሃብቶች በሚያስፈልጉት ቅድሚያ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያደርጋል።

ይህ ማለት ግን ለላቁ የደህንነት ሃይሎች ሚና የለም ለማለት አይደለም፣ ይህ ደቡብ አፍሪካ ከአፓርታይድ በሁዋላ ኮማንዶዎቹን በተመለከተ ማድረግ እየቻሉ ያመለጣቸው ነገር ነው። አዲሱን የተቀናጀው ሳንድፍ፣ ደቡብ አፍሪካ የአገሪቱን ኮማንዶ ስርአት በታተነቸው። ይህ የፓራ ወታደር ክፍሎች የከተማ ወይም የገጠር ማህበረሰቦችን ከተደራጁ ስጋቶች የሚጠብቀው የማህበረሰቡን ተሳትፎ በመጠቀም ነው። ምንጫቸው አፓርታይድ ስለነበር እንዲበተኑ ተደርገዋል። እንዳለመታደል ሆኖ፣ በመበታተናቸው የተነሳ በተፈጠረ ክፍተት ወንጀለኝነት በጣም አሻቅበዋል።[71]

**ትምህርት እና ስልጠና ላይ ማተኮር** የአፍሪካ ወታደሮች ከሚገጥማቸው ችግሮች አንዱ የትምህርት ብቃት እና የጦር ሜዳ ስልጠና ለእድገት እና ተጨማሪ ሹመት አለመታየታቸው ናቸው። ይህ መቀየር አለበት። ሙያዊ ብቃት ያለው ወታደር ትምህርት እና ስልጠና በጣም አስፈላጊ ነው። የደቡብ አፍሪካው ሳንድፍ መሰረታዊውን የስልጠና ፕሮግራም ለሁሉም ወታደሮች ተቋማዊ እንዲሆን ሲያደርግ ለሁሉም ኦፊሰሮቹ ሶስት የስልጠና ደረጃዎችን አካትቶዋል። የመቶ አለቃ ስልጠና የጨመረው ማህብረሰባዊነት (ወታደራዊ አስተሳሰብ)፣ የጦር መሳሪያ ግብግብ ስልጠና፣ እና የወታደር ትምህርት (የወታደሩን ሚና

በዘመናዊ ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መረዳት) ናቸው። የኮሎኔል ደረጃ ለማግኘት፣ ኦፊሰሮች የወታደር አመራር ካሪኩላን መማር ይኖርባቸዋል። በመጨረሻም፣ የጀነራል ደረጃን ለማግኘት፣ የኦፊሰሮቹ ካሪኩለም የሚያተኩረው ጀነራሎቹ እራሳቸውን በሚያገኙበት የፖለቲኮ ወታደር አካባቢ ነው።[72]

ትምህርት እና ስልጠና ወሳኝ ሚና የሚጫወተው በተለይ አስቸጋሪ ሃይሎችን ሰብስቦ ትጥቅ ማስፈታት፣ እንቅስቃሴ መገደብ፣ እና መልሶ ማዋቀር ላይ ነው። በቡሩንዲ ከጦርነት በሁዋላ ያለው ልምድ ያሳየው ሃይሎችን አቀናጅቶ ለተመሳሳይ ስልጠና ማብቃት ወደ ተሻለ የጋራ ልምዶች እና የዳበረ አንድነት አምርቶዋል።[73]

የወታደሩ ሚና እንደ አስተማሪነት የወታደሩን ስም በአጠቃላይ ህዝብ ዘንድ ያሻሽላል። ለአባሎቹ እኩል የሆነ የትምህርት ተደራሽነት በማቅረብ፣ አንድ ወታደር በማህበረሰቦቹ መሃከል የባለቤትነት መንፈስ በመገንባት የህዝብ ሃብቶችን በእኩልነት የማከፋፈያ ማሳያ መሆን ይችላል። የበለጠ የተማረ የደህንነት ሴክተር በበኩሉ ጥንቃቄን፣ ሚዛናዊነትን፣ እና ተለማማጅነትን በማሳየት በብዙ አፍሪካዊ የደህንነት ችግሮች ላይ ያሉ በማህበረሰቡ ላይ የተመሰረቱ ስጋቶችን ለመቋቋም ይቻላል።

በ 2010 ፣ በላይቤሪያ የተካሄደው ዳሰሳ የሚለካው ዜጎች፣ በጦር ሃይሎች ውስጥም ውጭም ያሉ፣ የወታደሩን የሙያ ክህሎት በ 6 አመታት ላይ በሁሉን አቀፍ የደህንነት ሴክተር ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ ያለውን እይታ ነው።[74] በአጠቃላይ፣ ውጤቶቹ ስለ ወታደሮቹ ሞራላዊ ስብእና እና ከሲቪል ማህበረሰቡ የሚያገኙት ክብር በጣም አዎንታዊ ነው። ወታደሮች እና ሲቪል ማህበረሰብ የወታደሩን እንደ ህዝብ ጠባቂነት እና የህግ መከበርን መረዳት ተመልክቶዋል። የጋራው መልእክት ለሰራዊቱ የቀረበው ትምህርት፣ በተለይ በህግ የበላይነት እና ሰብአዊ መብቶች ላይ፣ ለበለጠ ክብር እና ኩራት ላለው ወታደር አበርክቶዋል።

## ወታደሮች የሚሰሩበትን ሁኔታ ከፖለቲካ ነጻ ማድረግ

በሁሉም የአፍሪካ ህገ መንግስታት ውስጥ ያለው ክፍል እንደሚለው በሲቪል የተመረጠ ፕሬዚደንት ማለት የዋናው የታጠቀ ሰራዊት ኮማንደር ኢን ቺፍ ነው። ወታደሩን በሲቪል ለመቆጣጠር፣ ፖለቲከኞች በደህንነት ሴክተር ማሻሻያ ላይ የበለጠ ግልጽ መሆን አለባቸው። ይህም ወታደሩ

የሚሰራበትን ማእቀፍ ጨምሮ ይህም የሲቪል ማህበረሰቡ የራሱን እንዲያበረክት ያስችላል፡፡

የአፍሪካ ቻርተር በዲሞክራሲ፣ ምርጫ፣ እና አመራር ጥሩ የማነጻጸሪያ ነጥብ ነው፡፡ የሚያቀርበውም የዲሞክራሲያዊ እድገት መመሪያዎች እና ለህዝባዊ ተሳትፎ ክብር እንዲሁም የኢህገ መንግስታዊ የመንግስት ለውጦችን መከልከል ነው፡፡ ወደ መጨረሻው፣ የደህንነት ሴክተር መሻሻያ ድጋፍ በአጠቃላይ የሚውለው ለደህንነት መዋቅሩ ሲሆን፣ ትኩረቱ ወደ ፖለቲካዊ ተዋናዮች ሆነው የወታደሩ ፕሮፌሽናልነት ሊጫኑ ወደሚችሉትም መሆን አለበት፡፡

**የወታደር እና ፖለቲካዊ ተዋናዮችን ሚና መግለጽ** ፖለቲከኞች የወታደሩን ድጋፍ መፈለግ የሚያመለክተው ደካማ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት መኖር እና ይህም ለጥቅም ፈላጊ ፖለቲከኞች ወታደሩን ለመጠምዘዝ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ በፓለቲካዊ ጸባይ ዙሪያ ላይ ያሉ ጠንካራ ቅርጾች በወታደራዊ ፕሮፌሽናሊዝም ላይ ይህንን አሉታዊ ሚና ሊቀንሱ ይችላሉ፡፡

ለመጀመር፣ ሰልጣኝ ህግ አውጪዎች የሚቀበሉት የመከላከያ ፖሊሲ እና የውትድርና በጀት የሚጨምረው በሞራላዊ ኮርሶች ተሳትፎ እና ስለሙስና ያለው የጋራ መረዳት ሲሆን ይህም የጥሰቱ ጣጣዎች በግልስ መወያየት አለብን፡፡[75] ግልጽነት በመፍጠር ላይ ያለው ትኩረት ታማኝነትን ሲያጎለብት እንዲሁም በመንግስት ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ጸባይ በተሻለ ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡

የጦር ሃይሎች እና ፖለቲካ መጠላለፍ የቆየ ባህል ግልጽ የሆነ አሰራር ያላቸው የአፍሪካ ወታደሮች የሚሰሩበት ሁኔታ የማድረግን አስፈላጊነት በበቂ ሁኔታ አይገልጸውም፡፡ ህገ መንግስቱ እና የብሄራዊ መከላከያ ህጎች በግልጽ ማስቀመጥ ያለባቸው በጦርነት፣ በሰላም፣ እና በብሄራዊ ድንገተኛ ጊዜ የዕዝ ሰንሰለቱን ነው፡፡ በወታደሩ የውሳኔ ማሳለፍ ሚና ላይ የማያሻማ አረዳድ መኖር አለበት፤፤ ከተራው ወታደሩ ላይ የፖለቲካዊ ተሳትፎ እስከ የሲቪል ወታደሩ ግንኙነት የሚመራበት መንገድ ድረስ ያለው፡፡ ይህ ቅርጽ በተጨማሪም መያዝ ያለበት የብሄራዊ ደህንነት ሴክተር ህግ ዳሰሳ እና ክለሳ ሲሆን ይህም በደህንነቱ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ተቋማት ሚና እና ስልጣኖች ለመለየት እና ለማጥራት ይጠቅማል፡፡ ይህም የሚጨምረው የተሰየመ የድርድር ሂደት በተቋማት መሃከል እንዲሁም እነዚህን ተቋማት ለመጠምዘዝ በሚሞከሩት ፖለቲከኞች ላይ ነው፡፡

ከሽግግር በሁዋላ ባለው የቱኒዚያ መንግስት ለደህንነት ሴክተሩ ቅድሚያ ነገሮች ለመለየት ለመርዳት ባለው ሂደት፣ የጄኔቫ ማእከል ለታጠቁ ሃይሎች ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር በግልጽ ያስቀመጠው የአመርቂ፣ አስተማማኝ፣ እና ተጠያቂነት ያለው የደህንነት ሴክተር ቅርጽ ጥቅሞች እነዚህ ናቸው፤

- የያንዳንዱን ደህንነት ድርጅት ሚና እና አላማን መግለጽ
- የያንዳንዱን ደህንነት ድርጅት እና አባላታቸውን ስልጣን ስፋት እና ገደብ መግለጽ
- የውጭ ደህንነት ድርጅቶች የሚቆጣጠሩ ተቋማትን ሚና እና ስልጣን መግለጽ
- ለተጠያቂነት መሰረት ማቅረብ፤ ይህም በህጋዊ እና ህገወጥ ጸባይ መካከል ግልጽ መስመር ማስቀመጥ
- የህዝብ እምነት ማሻሻል እና የመንግስቱን እና የደህንነት ሃይሎችን ተአማኒነት ማጠናከር [76]

**ሲቪል-ወታደር ትብብር** ቅርጹ አንዴ በቦታው ከገባ፣ ወታደሩ ግልጽ እና ተባባሪ ፖለቲካዊ ሁኔታ ሲፈልግ ይህም ስልጣኑን በበጎ እንዲተገብር ይረዳዋል። ለምሳሌ፣ የሲቪል መሪዎች ለወታደር መሪዎች ፖለቲካዊ፣ ህብረተሰባዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ አማራጮችን ለመከላከያ በጀት የሚሆን ማስረዳት አለባቸው። በተመሳሳይ፣ ፖለቲካዊ መሪዎች የወታደር መሪዎችን ብቃት እና ምክር መጠየቅ ሲኖርባቸው ይህም የተለያየ የደህንነት ስትራቴጂ አቅጣጫዎችን ለማወቅ ይረዳል። ጠንካራ፣ ሁሉን አቀፍ የህግ አውጪ በመከላከያ ጉዳዮች ላይ ያለው ተሳትፎ ዲሞክራሲያዊ የሲቪል ወታደር ግንኙነት ጠቃሚ ማሳያ ነው።[77] በሰጥቶ መቀበል ላይ የተመሰረተ የቀስ በቀስ ለውጥ ሂደት ለስኬታማ ዲሞክራሲያዊ ትብብር እና በወታደሩ ላይ የሲቪሉ ቁጥጥር የማድረግ ተስፋዎችን አያሻሽልም።

ሌሶቶ እና ደቡብ አፍሪካ የሚያቀርቡት ምሳሌዎች ቅርጹን ለወሳኝ የደህንነት ድርጅቶች፣ እናም ከዛም አልፎ፣ የዲሞክራሲያዊ ሲቪል ወታደር ግንኙነቶች ናቸው። የመከላከያ ሃይል ህግ፣ በሌሶቶ ፓርላመንት በ1996 የጸደቀው፣ የሚያቀርበው ቅርጽ፣ ድርጅት፣ እና አስተዳደር እንዲሁም የታጠቁ ሃይሎችን ዲሲፕሊን የመሳሰሉትን ነው። የመከላከያ ሚኒስቴር በ1995 መቋቋም ተቋማዊ ያደረገው የሃይሎችን ቁጥጥር በሲቪል

እና በተመረጠ የሲቪል ባለስልጣን እንዲሁም የሃይሎችን ተጠያቂነት ለአመራሩ እና ለህግ አውጪው ቅርንጫፎች ነው፡፡ የታጠቁ ሃይሎች ከፓርቲያው ፖለቲካ መነሳት ወታደሩን ሃገራዊ ግዴታውን በመወጣት የበለጠ ፕሮፌሽናል ያደርጋል፡፡ ይህ መለያየት መንግስቱን የበለጠ ዲሞክራሲያዊ ያደርገዋል፡፡[78]

የደቡብ አፍሪካው ህገ መንግስት ያበረታታው በታጠቁ ሃይሎች፣ በፍርድ ቤቶች፣ እና በህግ አውጪው መሃከል ያለውን ንገግር ሲሆን ይህንን ያደረገው የደህንነት አገልግሎቶቹ አባላቶቻቸውን በአገሪቱ ህጎት እና ህገመንግስት መሰረት እንዲሰሩ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በተዛመደ መልኩ እንዲሰሩ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ሳንድፍ የተጠየቀው በመከላከያ ዴሞክራሲ ላይ ለወታደሩ እና ለመከላከያ ሚኒስቴሩ አባላት የሲቪክ ትምህርት ፕሮግራም እንዲቀርጽ እና ስራ ላይ እንዲያውል ነው፡፡[79] ይህ የሲቪል እና የወታደር አመራሩ የወታደሩን ስልጣን እና በማህበረስቡ ያለውን ሚና በደንብ እንዲያስቡበት ያበረታታል፡፡ በተጨማሪም ነጻ የመከላከያ ማሻሻያ ሂደት ያለው እና ከህዝቡ አስተያየት የሚጠይቅ፣ ይህም ወደ አዲስ የመከላከያ ፖሊሲ ከደቡብ አፍሪካ ብሄራዊ ደህንነት ቅድሚያዎች ጋር በደንብ የተያያዘ ፖሊሲ ለማውጣት ይመራል፡፡

**ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር ትብብር** ለብዙ የአፍሪካ አገሮች፣ አለም አቀፍ የደህንነት ሴክተር ማሻሻያ ድጋፍ ወሳኝ፡፡ አለም አቀፉ ማህበረሰብ በጣም የሚፈለግ ቴክኒካዊ፣ ህጋዊ፣ እና ፖለቲካዊ ድጋፍ ማቅረብ ሲችል ይህም ወታደሩ ከፖለቲካ እንዲወጣ እና ፕሮፌሽናል ክህሎቱን እንዲገነባ ነው፡፡ የመፈንቅለ መንግስት የማያዳግም ውግዘት እሱንም ተከትሎ በአካባቢው የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች (አርኢሲስ)፣ በ ኤዩ፣ እና በአለም አቀፍ ማህበረሰብ የሚደረግ ማእቀብ በጣም ወሳኝ ሲሆን ይህም በአፍሪካ ኣገራት የወታደሩን በፖለቲካዎች ጉዳይ ጣልቃ ገብነት ይከላከላል፡፡ በተጨማሪም የአፍሪካ ዴሞክራሲዎች በቀጥታ የዲሞክራሲያዊ ደህንነት ክፍል ተጠያቂነት በመደገፍ ረገድ በቀጥታ እንዲሳተፉ ያስፈልጋል፡፡ የደህንነት ክፍል ማሻሻያ ድጋፍ ከአጋሮች፣ እንደ ቦተስዋና፣ ህንድ፣ እና ደቡብ አፍሪካ፣ የሌሴቶን ዴሞክራሲያዊነት ሂደት ለመደገፍ፣ እና በሌሴቶ መከላከያ ሃይል ያለውን ዲሲፕሊን ለማጠናከር ያግዛል፡፡[80]

ንቁ እና ግንዛቤ ያለው የሲቪል ማህበረሰብ፣ በተመሳሳይ፣ የዲሞክራሲያዊ እሴቶች እንዲያድግ ሲረዳ የወታደር እንደፈለገ መሆንን

ይገታል። ሲቪል ማህበረሰቦች ንቁ እና ከምርጫ በሁዋላም ተሳትፎ የሚያደርጉበት አካባቢ መፈንቅለ መንግስቶች የመፍረስ እድላቸው ሰፊ ነው። የማህበረሰቡን አቅም በመጨመር፣ አንድ ሀገር ተጠያቂነት እና ግልጽነት መጨመር ይችላል። ነጻ ሚዲያ ለተሳለጠ ሰፊ የህዝብ ውይይት በደህንነት ሴክተር ላይ እና በወታደር ጉዳዮች ላይ ለማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህ ሂደት በተጨማሪም በማህበረሰቡ፣ በስቴቱ፣ እና በታጠቁ ሃይሎች መሃከል መተማመን ይገነባል።

በላይቤሪያ፣ ለምሳሌ፣ ፕሬዚደንት ኤለን ጆንሰን ሰርሊፍ መንግስታቸው የሲቪል ማህበረሰብን በጦርነት በታመሰቸው አገር ውስጥ በመገንባት ረገድ ትልቅ እምርታ አሳይተዋል። በ 2010 ፕሬዚደንት ጆንሰን ሰርሊፍ የመረጃ ነጻነት ህግን በማጽደቅ የመንግስት ግልጽነት እና ተጠያቂነት ለህዝቡ እንዲሆን አድርገዋል።[81] በሚዲያ፣ አጠቃላይ ህዝቡ ስለደህንነት ሴክተር ያለውን የማሻሻያ ሂደት ተገንዝበዋል። ስለ ህግ የበላይነት እና የወታደሩ ሚና አገርን በመጠበቅ እና ሰብአዊ ደህንነት ትምህርቶች በሬዲዮ ፕሮግራሞች ለአጠቃላይ ህዝቡ ትምህርት ተሰጥቶዋል። ይህም መነሳሳት ያላቸው ምልምሎችን ማምጣት ብቻ ሳይሆን ህዝቡን እንዴት የወታደራዊ ግለሰቦችን ተጠያቂ ማድረግ እንደሚችሉ ያሳስባል።[82]

እንደ አንድ ላይቤሪያዊ ወታደር:

> በአሁን ጊዜ በዚህ አለም ላይ ወታደር ሰው በፍትሓ ብሄር ህጎች አይዳኝም። ይህም ሲሆን እዚህ (ህዝብ) ጋር ስንወጣ ጸባይ እንድንገዛ እንመከራለን። የማይሆን ነገር ከሰራህ፣ በፖሊስ ልትታሰር ትችላለህ፤ እናም ፖሊስ ጥፋተኛ ሆኖ ካገኘህ፣ ወደ ፍርድ ቤት ሄደህ ይፈረድብሃል። ይህ በዱሮ ወታደር ጊዜ ያልነበረ ሲሆን በአዲሱ ወታደር ነገሮች የተለዩ ናቸው።[83]

በብዙ የአፍሪካ አገሮች ለመረጃ ነጻነት ህጋጋት ለማሳለፍ ዘገምተኛ ናቸው። በተጨማሪም፣ እነዚህ ህጎች በሚሰሩበት ቦታ፣ ተቃውሞው ጠንካራ ሆኖ ቆይቶዋል። ሞሪታኛ የፕሬስ ነጻነት ህግ በ 2011 ስታሳልፍ ይህም የጋዜጠኞችን መታሰር አስቀርቶዋል። ሆኖም፣ ጋዜጠኞች የተሳሳተ

መረጃ ወደ ሁከት እና ብጥብጥ የሚመራ እና የታጠቁ ሃይሎችን ዲሲፕሊን የሚረብሽ ከሆነ ሊቀጡ ይችላሉ።[84] በተመሳሳይ፣ ምንም እንኳን በ 2011 የመረጃ ነጻነት ህግ ከአስር አመት አተያይ ከወጣ በሁዋላም፣ የናይጄሪያ መንግስት በህጉ መሰረት ያሉ ጥያቄዎችን ባለማክበሩ ከፕሬሱ ውግዘት ደርሶበታል።[85] በደቡብ አፍሪካ፣ በህገ መንግስቱ ላይ የመረጃ ነጻነት ቢኖርም፣ ፓርላመንቱ በ 2011 የመንግስት ምስጢሮች ባላቸው ነገሮች ላይ መዘገብን የሚገድብ ህግ አውጥቶዋል፤ ምንም እንኳን ህጉ በፕሬዚደንት ዙማ በ 2013. ላይ ተቀባይነት ቢያጣም።[86]

በምስጢራዊ ስራዎች፣ ባልተገለጹ በጀቶች፣ እና በጀርባ የሃይል ውሎች፣ ብዙ የአፍሪካ ወታደሮች ከሲቪል ማህበረሰቡ እና ከሚዲያው ጋር ያላቸውን የተበላሸ ግንኙነት ለማደስ ብዙ ስራ ይጠብቃቸዋል። እናም የሚቀያየረው አላማ የሚጠይቀው ወታደሩ ከሲቪሉ ጋር በተደጋጋሚ እንዲገናኝ ሲሆን፣ የአፍሪካ ወታደሮች ከሚዲያ ጋር እንዴት መነጋገር እንዳለባቸው መማር በጣም አስፈላጊ ነው። በጠጋኝ ግንኙነት መገንባት ላይ ያነጣጠረ የሚዲያ ስልጠና በአፍሪካ ወታደሮች እና በአጠቃላይ ህዝብ መካከል ያለውን አለመተማመን ለመቀነስ ረጅም ርቀት ይሄዳል።

## ግብረ ገብነት እና ተጠያቂነትን ወደ ወታደሩ ባህል ተቋማዊ ማድረግ

ደህንነት የወታደሩ ስራ ብቻ አይደለም። የሚጨምረው ሌሎች ሚኒስቴሮች፣ የዳኝነት አካል፣ የህግ አውጪው አካል፣ እና የሲቪል ማህበረሰቡንም ነው። ስለዚህ፣ ሙያዊ ብቃት ያለው ወታደር ከሁሉም ቁልፍ የደህንነት ተዋናዮች ጋር ግንኙነቱን በመጠበቅ ስራዎቹን በብቃት መስራት አለበት። ወታደሩ፣ ሞራላዊ እና ተጠያቂነት ባህሉን ተቋማዊ የማድረግ ግዴታ ሲኖርበት ይህም የማህበረሰቡን እምነት እና ክብር እንዲያገኙ ያደርጋል።

**የወታደሩን ዲሲፕሊን እና ስራ ማጠናከር** የአፍሪካ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች በአጠቃላይ የተዝረከረኩ እና የሰብአዊ መብት ረጋጭዎችን በመክሰስ ረገድ ውጤታማ ያልሆኑ ናቸው። ለውትድርና አመራር መጠከር ያለበት የወታደሩን የፍርድ ቤት ሲስተም በአፍሪካውያን ጦር ሰፈር ውስጥ ዲሲፕሊንን ለማስመለስ እንዲጠቅም ነው።

ለመጀመር ያህል፣ የአፍሪካ ወታደሮች የወታደር ፍትሕ ሲስተም የሚመሩትን የሁኒፎርም የወታደር ፍትሕ ህጎች (ዩሲኤምጄ) ን አሰራር እና አመራር ህጎችን በድጋሚ ማየት ይኖርባቸዋል። ዩሲኤምጄ የሚያቀርበው ግልጽ መመሪያ ከትናንሽ የረብሻ ጥፋቶች እስከ በጣም ከባድ ጥፋቶች ነፍስ ማጥፋትን ጨምሮ ያጠቃልላል። የተለመደው፣ በመጨረሻ የተጠቀሰው ጥፋት በችሎት ሲስተም ይስተናገዳል። የጣልቃ ገብነት አስተያየቶችን ለመገደብ፣ አመራሩ ከወታደር ሰንሰለት እዝ ውጪ የሆነ ነጻ በሆነ መንገድ የሚታዩ የተወሰኑ ወይም ሁሉም የወንጀል ክሶችን ለማየት ቢሞክር ይመረጣል።

የወታደሩ የፍትሕ ስርዓት ከሰብኣዊ መብቶች ደረጃዎች ጋር መጣጣማቸውን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው።[87] በአብዛኛው የአውሮፓውያን የወታደር ህጎች የተሰሩት በአውሮፓ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተመሰረተ ነው። የአፍሪካ ቻርተር በሰብኣዊ እና በህዝባዊ መብቶችም የሚያቀርበው ተመሳሳይ የማነጻጸሪያ ህግ ሲሆን የወታደሮች ፍትሕ ስርኣት ከሃገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ህጎች ጋር አብረው መሄዳቸውን ያረጋግጣሉ። የህግ ብቃት በአገር ውስጥ ከሌለ፣ መንግስታት እና ወታደሮች ከአርኢሲዎች፣ ከኤሁ፣ እና ከአለም አቀፍ አጋሮችን መፈለግ አለባቸው።

አነስ ላሉ ጥፋቶች፣ የወታደሩ ዲሲፕሊን ቦርዶች በብዛት ሊያገለግሉ ይችላሉ። በላይቤሪያ፣ የወታደሩ የፍትሕ ስርኣት በአብዛኛው ጉዳዮች ላይ ከሌለ፣ ሁሉም የወንጀል ጉዳዮች የተሙዋላ የሚሰር የማርሻል ፍርድ ቤት ስርኣት እስኪዘረጋ ድረስ በሲቪል ፍርድ ቤቶች እንዲታይ ተወስኖዋል።[88] ይህ አሰራር ለሌሎች ከግጭት በሁዋላ ላሉ እንደ ኮትዲቩዋር በወታደሩ ሂደት ላይ እየተካሄደ መሻሻል ላይ የሚፎካከሩ ግፊቶች ምክኒያት እንዲተገበሩ ሊጠቅም ይችላል።

በከሰሃራ በታች ባሉ ሃገሮች ባሉ የጦር ሰፈሮች የሚታየው ጋጠ ወጥነት እና ፍትሕ አልባነት የተወሰኑ የወታደር ዲሲፕሊን ቦርዶች የብቃት ማነስ ማሳያ ነው። በአብዛኛው፣ ስርአቱ ወጥ ያልሆነ እና በተለይ ቱባ ባለስልጣናትን የሚነኩ ጉዳዮች ላይ የሚያዳላ ነው። ፍትሓዊ ያልሆነ እና የሚያዳላ ፍርዶች ላይ አንድ ወታደር ይግባኝ ማለት አለመቻል ቦርዱን ያሳጣዋል። በዩሲኤምጄ ውስጥ በወታደሩ ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ ሚኒስቴር ላይ ለፍትሕ መረጋገጥ ወታደሩ ይግባኝ የማለት እንዲኖረው አንቀጾች መግባት አለባቸው።

**ታማኝነትን መሸለም እና ተጠያቂነትን ማጠናከር** የወታደር ስነ ምግባር ባህል መፍጠር የሚያካትተው በታጠቁ ሃይሎች ያለውን ማበረታቻ መለወጥን ነው። ታማኝነት በሰራተኛ እድገት፣ ቅጥሮች፣ እና ሽልማቶች ላይ ዋና መመዘኛ መሆን ያለበት። ይህም ስራ ላይ ሊውል የሚችለው የሰብአዊ መብቶች እሴቶች እና የስነ ምግባር ደንቦች፣ ስልጠና እና ትምህርትን በማጠናከር ነው።[89]

በተመሳሳይ፣ የሙስና እድሎች ማነስ አለባቸው። ከመጠን ጋር ሳይያያዝ፣ የወታደር አቅራቢ ቢሮዎች የሚጠይቁት የበቁ ፕሮፊሽናሎችን እና የጠበቀ የአካሄድ ቅርጽን በጥብቅ መከተልን ነው። ግዢ ፕሮፌሽናል የሆነ ክህሎት ነው። ስለዚህ፣ ሚኒስትሮች ጠንካራ የግዢ ሙያተኞችን መገንባት አለባቸው። የብዙ አገሮች ልምድ የሚያሳየው የተማከለ የግዢ ቢሮ (ለሁሉም አጠቃላይ የታጠቁ አገልግሎቶች አንድ) ከወታደሩ ውጪ ይህም በብዛት ለሚወዘበሩ ቦታዎች ተጨማሪ የተጠያቂነት ከለላ ይፈጥራል። የግዢ ውሳኔዎችን በተዋረድ ስርኣት በወታደሩ ማድረግ ለበላይ ባለስልጣናት የግዢ ሂደቱን እንዲጫኑ እድል ይሰጣል። የሲቪል ማህበረሰቡን ማሳተፍ (በቁጥጥር መልክ ወይም በፕሮቶኮል ውስጥ በማሳተፍ) በተለይ ለሙስና በተጋለጡ ቦታዎች ላይ እንደ ግዢ የመሰሉ፣ የሂደቱን ግልጽነት እና ታማኝነት ይጨምራሉ።

ብዙ በአፍሪካ ወታደሮች ውስጥ ያሉ ውስጣዊ ችግሮች የወታደሮቹን ቁጥጥር አገልግሎቶች የመቆጣጠር ሚና ቢጠነከሩ እና ራሳቸውን ቢችሉ ይቀረፍ ነበር። ለቀድሞው የታጠቁ ሃይሎች ጠቅላይ መሪ ወይም ትልቅ ባለስልጣን ቢሮ ከመሆን ይልቅ፣ የቁጥጥር አገልግሎቶች ክፍል በወታደር እና ሲቪል ተቆጣጣሪዎች፣ በጠበቃዎች፣ እና በፖሊሲ መርማሪዎች ቢሞላ እና እነሱም ባላቸው ስልጣን በታጣቂው ሃይሎች ሁኔታ ላይ ሪፓርት ቢያቀርቡ ጥሩ ነው። እነዚህ ሪፖርቶች ለፖሊሲ እና አስተዳደር ጥቅሞች እንዲሁም በባለስልጣኖች እና በአስተዳዳሪዎች ስለ እድገት፣ ቅጥር እና ሽልማቶች ላይ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።

እነዚህ አሰራሮች ስራ ላይ መዋል ያለባቸው በደንብ በተወሰነ የስነ ምግባራዊ ቅርጽ እና የሞራል፣ የእሴቶች፣ እና ከወታደሩ የሚጠበቁትን ጸባዮች ያገናዘበ በሆነ መልኩ ነው። ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በዚህ ቅርጽ አምስት ቁልፍ ክፍሎችን ለይቶዋል፣

- አንድ ነጠላ፣ በቀላሉ የሚገኝ የስነ ምግባር ደንቦች ለሁሉም ሰራተኞች፣ በሞራል እና እሴቶች በጥልቀ የተገነባ፣ ተደራሽ የሆነ (ህግ ነክ ያልሆነ) ጽሁፍ
- በተጠያቂነት ላይ ግልጽ መመሪያ፣ ለሞራል መርሃ ግብሩ ተጠያቂ ማን እንደሆነ፣ የሚጠረጠሩ የሙስና ጉዳዮችን እንዴት ሪፓርት እንደሚደረግ እና ተጨማሪ ምክር የት እንደሚገኝ
- በጉቦ፣ ስጦታ፣ እንክብካቤ፣ የጥቅም ግጭት፣ እና ከመለየት በሁዋላ ያሉ ክንውኖች (ውትድርናውን በለቀቀ ግለሰብ) ላይ ያሉ መመሪያዎች፣ ቢቻል ከተጠኑ ጉዳዮች ጋር
- የተለመዱ የስነ ምግባር ስልጠና እና የድጋሚ ኮርሶች ህጎቹን በተግባራዊ ሁኔታዎች ላይ የሚገልጹ
- የህጉን እና የማስፈጸሚያ መርሃ ግብሩን በየጊዜው የሚደረጉ ማሻሻያዎች [90]

የአለም አቀፉ ማህበረሰብ የወታደር ጉዳዮችን በማስተዳደር እና በመቆጣጠር ረገድ ስልጠና በማድረግ ሊያግዝ ይችላል። የአፍሪካ ወታደሮች እርስ በርሳቸው ስለተማሩት ነገር ሊካፈሉ ይችላሉ፤ ልክ እንደ አፍሪካ የመመማሪያ መድረክ አይነት፣ ይህም በአገር አባሎቻቸው ምርጥ ልምዶችን መካፈል ይችላሉ። ከነዚህ ትብብሮች የተገኘውን ትምህርቶች፣ ቴክኒኮች፣ እና አሰራሮች ተቋማዊ ለማድርግ፣ የአፍሪካ ወታደሮች የመማማሪያ ማእከል በየወታደር ኮሌጆቻቸው መመስረት ይኖርባቸዋል።

**የወታደር እንባ ጠባቂ እንደ ነጻ የወታደር ቁጥጥር መንገድ መፍጠር** የወታደር ማሻሻያዎች በብዛት ከላይ ወደታች የሆኑ፣ ከውስጥ የሚወጡ ሂደቶች ሲሆኑ፣ የብዙ ተራ ወታደሮች እና ዜጎችን ከጨዋታ ውጭ ያደርጋሉ። የተቀናጀ የወታደር ቁጥጥር መንገድ እንደ የቁጥጥር አገልግሎቶች ክፍል አይነት ማለት ወታደሩ ለራሱ ቁጥጥር ሃላፊነት እንዳለበት፣ ይህም የጥቅም ግጭት በቀላሉ ፈጥሮ ጠቃሚነቱን ይቀንሳል።

ለቁጥጥር አገልግሎቶች አማራጭ ወይም አጋዥ የሚሆነው ነጻ የወታደር እንባ ጠባቂ ወታደሩን የመልካም አስተዳደር አሰራሮችን እንዲገነዘብ ይረዳል። ወታደሩ ላይ ብቻ ያተኮረ ነገር ግን በሲቪሎች የሚሰራ፣ ነጻ እና የማያዳላ እንዲያደርግ ይረዳል። በካናዳ እና ጀርመን፣ የወታደር እንባ ጠባቂ የሚመለከተው ስላልተገቡ እና ጨቋኝ ጸባዮች እንዲሁም የውትድርና አሰራር ድክመቶችን ከዛም አልፎ የማስተካከያ እርምጃዎችን በሪፓርት ማቅረብ ለወታደሩ ብቻ ሳይሆን ለህግ አውጪው እና ለህዝቡም ጭምር

ነው፡፡[91] ውጤታቸውም የወታደሩን ብቃት ማሻሻል ይህም ተጠያቂነትን እና መላሽነትን ማስፈን ነው፡፡

ከአህጉሩ ግማሽ በላይ አገሮች የእንባ ጠባቂ ቢሮ ሲኖራቸው ነገር ግን በአብዛኛው የሚያተኩሩት በሲቪሉ ቁጥጥር ላይ ነው፡፡ እንደ ህግ አውጪው፣ ብዙዎቹ ከመከላከያ ሴክተሩ ጋር ለመስራት አስፈላጊ ብቃት የላቸውም፡፡ የወታደር እንባ ጠባቂ ቢሮን ለማሰራት ቁልፉ ነገር የአሰራር ነጻነት ነው፡፡ ከወታደር ሰራተኛው ተነጥሎ የሚገኝ ይህም ምርምሮችን እና ሪፖርት ማሳተሙን ከሌሎች የመንግስት ክፍሎች ውጪ በነጻነት መስራት እንደሚያስችለው ነው፡፡ የገዘፈ የፖለቲካ ስልጣን ሊኖረው ሲገባ፤ ይህም ከህጋዊ ስልጣን እስከ ምርምር ለመስራት የሚያስፈልገውን መረጃ እስከ ማግኘት እስከ ኦፊሴላዊና የህዝብ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ለሲቪሉ እና ወታደሩ አመራር አስተያየት እስከመስጠት ይጨምራል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ህጋዊ፣ የምርመራ እና የምርምር ልምድ ከመከላከያ ሴክተር ጋር የተገናኘ እንዲሁም ከፍተኛ የደህንነት ይለፍ ያላቸው ሲቪል ግለሰቦች ይህንን ቢሮ ላይ መስራት አለባቸው፡፡

በወታደር እንባ ጠባቂ ቢሮ የሚታተሙ ግኝቶች እና አስተያየቶች የፓርላማውን ቁጥጥር እንዲጠናከር እና የበለጠ ግልጽነት እና ተጠያቂነት በወታደሩ ላይ እንዲኖር ይረዳል፡፡ የወታደር እንባ ጠባቂ፣ በተመሳሳይ፣ የዜጎች ፍላጎቶች ከጸባይ ነክ ክሶች እስከ በወታደር አሰራር ላይ ስላሉ ክፍተቶች ለመለየት ማሳያ መሳሪያ ሊሆን ይችላል፡፡

**የፓርላማውን ቁጥጥር ማጠንከር እና ውጫዊ ኦዲቶችን ተቋማዊ ማድረግ** ሙስና እና ብልሹ አስተዳደር በወታደሩ ውስጥ ለብሄራዊ ደህንነት እና በአጠቃላይ በመንግስቱ ላይ ያለውን መተማመን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ስላላቸው፣ ውጫዊ ኦዲቶች በህዝብ ንብረት አስተዳደር ላይ የሆኑትን የብሄራዊ ቅድሚያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የፓርላማውን ቁጥጥር በመከላከያ ግዢ ላይ ማጠንከር የወታደሩን ውስጣዊ አመራር ሊያሻሽል እና የተጠያቂነትን ችግር ለመፍታት ረጅም ርቀት ሊሄድ ይችላል፡፡ በአብዛኛው የአፍሪካ ህግ አውጪዎች የንብረቶችን አጠቃቀም ለመቆጣጠር እና የመከላከያ ሀብቶች በደንብ ስራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ህገ መንግስታዊ ስልጣን አለው፡፡ በደቡብ አፍሪካ፣ ህግ አውጪዎች በውትድርና ግዢ ላይ ስልጠና ወስደዋል፡፡ በተጨማሪም፣ ብቁ ባለሙያዎች በፓርላማ ኮሚቴዎች ውስጥ ሲካተቱ ይህም ክርክሩን

እና ድርድሩን ወደ ፊት ለማስኬድ ያግዛል። ደቡብ አፍሪካ እና ዩጋንዳ ሚኒስቴሮችን ተጠያቂ ለማድረግ በህዝብ አስተያየቶች ላይ ይተማመናሉ። ይህ የህግ አውጪው ቁጥጥር የቁጥጥር አገልግሎቶች ወይም የወታደር ውስጣዊ ቁጥጥሮች እና የመከላከያ ሚኒስቴር በሚወድቅበት ጊዜ ሙስናን እና የህዝብን ገንዘብ አላግባብ ማዋል እንዳይኖር ወሳኝ መከላከያ መንገዶች ናቸው። ይህም የተወሰነ ስራ እንደሚጠይቅ ጥርጥር የለውም፣ በተለይም በወታደር ጉዳዮች ላይ የሲቪሎች ተሳትፎ ኖሮ በማያውቅባቸው ሃገሮች ላይ። ነገር ግን ጠንካራ የሲቪል ቁጥጥር መገንባት የወታደር ሙያ ክህሎት የማስረጽ ወሳኝ አካል ናቸው።

ብዙ የወታደር መሪዎች በንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊዎች ናቸው፣ ይህም ካላቸው የደህንነት ስልጣን ጋር ግጭት መፍጠር ብቻ ሳይሆን ያልተገለጸ ገንዘብ ከህዝቡ ወደ ወታደሩ ሊያሸጋግሩ ይችላሉ። ከፍተኛ የወታደር መሪዎች የጥቅም ግኝት አለመኖሩን ለማሳየት እና ቁጥጥሩን ለማቃለል በየአመቱ ያላቸውን ሃብት እንዲያስመዘግቡ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። የፓርላማ ጥያቄ ወይም የእውነት ፍለጋ ስራ የወታደሩን ገቢ እና ወጪ ለመለየት እና ለመቆጣጠር ሌላ ጠቃሚ መሳሪያ ነው።[92] የመከላከያ ወጪዎች ላይ የሚያተኩሩ የጸረ ሙስና መርሃ ግብሮች የመንግስትን ወጪ አመራር በአጠቃላይ ያሻሽላሉ። እነዚህ ስራዎች ፉክክርን፣ ግልጽነት፣ እና የግዢ ቁጥጥርን ሲያመጡ የጥቅም ግንኙነትን ይቀንሳሉ። ለብሄራዊ የደህንነት ጥቅሞች ሲባል የመከላከያ በጀትን በሚስጥር ማቆየት የወታደሩን ደካማ አመራር ለመደበቅ ምክኒያት ሊሆን አይገባም። መከላከያ የህዝብ አገልግሎት ነው፣ ስለዚህም ህዝቡ በወታደሩ እንዴት እና ለምን በጀቱ እንደወጣ ማወቅ ይኖርበታል።

# ማጠቃለያ

የአፍሪካን ወታደሮች ሙያዊ ክህሎት ፕሮፌሽናል ማድረግ ላይ ያሉት ችግሮች እጅግ በጣም ብዙ ቢሆኑም ማድረግ የማይቻሉ ግን አይደሉም። የጎሳ እና የብሄር ማዳላቶች፣ አንዳንድ ሰራዊቶች ከቅኝ ግዛት ወቅት የወረሱዋቸው፣ በ አንድ (ጎሳዊ፣ ፖለቲካዊ) ቡድን ስልጣን በሃይል ለመያዝ ወይም ለማቆየት እና በሌሎች ወጭ ላይ በመመርኮዝ ለራሳቸው ጥቅም ተሰርቶባቸዋል። በአፍሪካ ላሉ ታዳጊ አገሮች፣ ወታደሩ፣ ለአገሪቱ መከላከያ እና ጥበቃ ሃላፊነት እንዳለበት ተቋም፣ አገራዊ እና ሪፑብሊካዊ መሆኑ

ወሳኝ ነው፡፡ ለዛም፣ ከፖለቲካ ውጪ መሆን እና ለአላማው እራሱን የሰዋ መሆን አለበት፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ፣ በወታደሩ ያለው የህገ መንግስታዊ ትእዛዝ፣ እና ጸባይ ከህግ የበላይነት በተጻረረ መልኩ መሆኑ በወታደሩ እና በፖለቲካ አመራሮቹ መፈጸሙ በአፍሪካ የተለመደ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሊከላከልለት በሚገባው በህዝቡ አይን የወታደሩን ታማኝነት ያሳንሳል፡፡ ይህም በአፍሪካ የወታደሩን ሙያዊ ብቃት ለመጨመር እና በአፍሪካ የዲሞክራሲያዊ ስርጸትን ለማጎልበት ያለው እንቅስቃሴ ስለሚጻረር ይህንን አካሄድ መቀልበስ ያስፈልጋል፡፡

በሜዳው ውስጥም፣ የአፍሪካ ወታደሮች ኣላማዎቻቸውን በብቃት ለመወጣት የስራ ብቃት ያጥራቸዋል፡፡ አንዳንዱ በውስን ሃብቶች ምክኒያት ሲሆን፣ ይህም ቅርጾችን እና አላማዎችን አፍሪካ ከሚያጋጥሙዋት የደህንነት ችግሮች ጋር ያልተጣጣሙ ነገሮች፣ በተለይም የአገር ውስጥ ወይም ሃገር ተሻጋሪ ያልሆኑ ስጋቶች ለደካማ ስራ እና ብቃት ምክኒያት የሆኑ ናቸው፡፡ የአፍሪካ የታጠቁ ሃይሎች ለዚህም ሲባል በደንብ በመደራጀት ለነዚህ ስጋቶች ያላቸውን የመከላከል ብቃት እንደ ስትራቴጂያዊ የደህንነት ቅርጽ አካል ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

ነገር ግን የወታደር ሙያ ክህሎት ከአስተዳደር ሃሳብ በላይ ነው፡፡ ህብረተሰቦች ለወታደሮቻቸው የሚያስተላልፉት ልዩ ሃላፊነት ነው፡፡ የህብረተሰቡ መረጋጋት እና ልቀት የሚመረኮዘው ራሳቸውን በዲሲፕሊን እና በክብር መልኩ ለሚመሩ ወታደሮች ነው፡፡ በአፍሪካ ወታደሮች ያላቸው የሙያ ክህሎት የሚጀምረው መሰረታዊ ከግብረ ገብ እሴቶች ነው፡፡ በአፍሪካ የወታደር ሰራተኞች በትንሹ እሴት እና ጸባይ ለአገሪቱዋ እና ለህገ መንግስቱ ታማኝነታቸውን ማሳየት፣ ለዲሞክራሲያዊ የሲቪል ባለስልጣናት መታዘዝን፣ የሃላፊነት ስሜትን፣ እና ለህግ የበላይነት ማክበርን ነው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ መመሪያዎች ከተከተሉ፣ የአፍሪካ ወታደሮች የበለጠ ሙያዊ ብቻ ሳይሆን ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ለተሻለ ደህንነት እና ዲሞክራሲያዊ የአህጉሩ አመራር ማበርከት እንዲሁም በዜጎች አይን አዲስ ክብር ይጎናጸፋሉ፡፡

# ማስታወሻዎች

[1] Camille Dubruelh and Mathieu Olivier, "L'Afrique n'est plus seulement un acteur passif dans le trafic de drogue. La consommation augmente." *Jeune Afrique*, April 24, 2012. Adam Nossiter, "U.S. Sting That Snared African Ex-Admiral Shines Light on Drug Trade," *The New York Times*, April 15, 2013.

[2] "Nigeria: Massive Destruction, Deaths from Military Raid," Human Rights Watch, May 1, 2013.

[3] Jeffrey Gettleman, "Elephants Dying in Epic Frenzy as Ivory Fuels Wars and Profits," *The New York Times*, September 3, 2012.

[4] Daniel Howden, "Terror in Nairobi: The Full Story Behind al-Shabaab's Attack," *The Guardian*, October 4, 2013.

[5] Samuel E. Finer, *The Man on Horseback: The Role of the Military in Politics* (New Brunswick, NJ: Transaction Publishers, 2002).

[6] Zoltan Barany, *The Soldier and the Changing State* (Princeton: Princeton University Press, 2012), 1.

[7] Habiba Ben Barka and Mthuli Ncube, "Political Fragility in Africa: Are Military Coups d'Etat a Never-Ending Phenomenon?" African Development Bank (September 2012), 3.

[8] Stefan Lindemann, "The Ethnic Politics of Coup Avoidance: Evidence from Zambia and Uganda," *Africa Spectrum* 46, No. 2 (2011), 4. For background on datasets used by Lindemann and other authors to identify the number of coups, see Jonathan M. Powell & Clayton L. Thyne, "Global instances of coups from 1950 to 2010: A new dataset," *Journal of Peace Research* 48, No. 2 (2011), 249-259. Powell and Thyne identify the varying definitions of "coup d'état" to explain for the variances in reported instances of attempted and successful coups.

[9] Barka and Ncube, "Political Fragility in Africa," 4.

[10] Ibid., 9.

[11] Mathurin Houngnikpo, *Africa's Militaries: A Missing Link in Democratic Transitions*, Africa Security Brief No. 17 (Washington, D.C.: National Defense University Press, January 2012).

[12] Samuel P. Huntington, *Political Order in Changing Societies* (New Haven: Yale University Press, 1968).

[13] Barka and Ncube, "Political Fragility in Africa," 9.

[14] Rafael Marques de Morais, "The Angolan Presidency: The Epicentre of Corruption," *Pambazuka News* No. 493, August 5, 2010, available at <http://www.makaangola.org/wp-content/uploads/2012/04/PresidencyCorruption.pdf>.

[15] Emmanuel O. Ojo, "Taming the Monster: Demilitarization and Democratization in Nigeria," *Armed Forces & Society* 32, No. 2 (January 2006), 254-272.

[16] Plato, *The Republic*, tr. G.M.A. Grube (Hacket, 1992), 417b and 434a-b.

[17] "Above the State: The Officers' Republic in Egypt," Carnegie Middle East Center, August 1, 2012.

[18] Zeinab Abul-Magd, "The Army and The Economy in Egypt," *Jadaliyya*, December 23, 2011, available at <http://www.jadaliyya.com/pages/index/3732/the-army-and-the-economy-in-egypt>.

[19] David D. Kirkpatrick, "Egyptians Say Military Discourages an Open Economy," *The New York Times*, February 17, 2011.

[20] Yezid Sayigh, "Morsi and Egypt's Military," *Al-Monitor*, January 8, 2013, available at <http://www.al-monitor.com/pulse/originals/2013/01/morsi-army-egypt-revolution.html>. Under the 2014 constitution created after the military ousted Morsi, the NDC has 14 members of which 8 are military.

[21] Kirkpatrick, "Egyptians Say Military Discourages an Open Democracy."

[22] Erin Cunningham, "Egyptian Authorities Detain Thousands Amid Crackdown on Dissent," *The Washington Post*, March 10, 2014.

[23] Abigail Hauslohner, "Egypt's Military Expands Its Control of the Country's Economy," *The Washington Post*, March 16, 2014.

[24] Dan Henk, "The Botswana Defence Force: Evolution of a Professional African Military," *African Security Review* 13, No. 4 (2004), 92.

[25] Ibid., 98.

[26] Boubacar N'Diaye, "Mauritania," in *Security Sector Governance in Francophone West Africa: Realities and Opportunities*, eds. Alan Bryden and Boubacar N'Diaye (Geneva: Geneva Center for the Democratic Control of Armed Forces (DCAF), September 2011), 152-153.

[27] Comi M. Toulabor, "Togo", in Ibid., 232.

[28] Stefan Lindemann, "Civilian Control of the Military in Tanzania and Zambia: Explaining Persistent Exceptionalism," Crisis States Working Papers Series No. 2 (London: Crisis States Research Centre, 2010), 3.

[29] Barany, *Soldier and the Changing State*, 276.

[30] Ibid., 288.

[31] Lindemann, "Civilian Control of the Military," 12.

[32] Cyrus Samii, "Perils or Promise of Ethnic Integration? Evidence from a Hard Case in Burundi," *American Political Science Review* 107, No. 3 (August 2013).

[33] *Midterm Report from the Group of Experts on Côte d'Ivoire prepared in accordance with paragraph 16 of Security Council resolution 2045* (2012). United Nations (S /2012/766), October 15, 2012.

[34] Library of Congress Country Studies, Ivory Coast – Chapter 1, Historical Setting – Consolidation of Power in the 1960s and 1970s, Library of Congress Call Number DT545.22 .C66 1990.

[35] Raphaël Ouattara, "Côte d'Ivoire," in Bryden and N'Diaye, *Security Sector Governance in Francophone West Africa*, 74.

[36] "Guinea: Victims of Security Forces Crackdown," Situation Report No. 3, UN Office for the Coordinator of Humanitarian Affairs, October 18, 2009, available at <http://reliefweb.int/sites/reliefweb.int/files/resources/E13FEB1A6E2B72AEC125765400425D46-Full_Report.pdf>.

[37] Adam Nossiter, "Bodies Pour In as Nigeria Hunts for Islamists," *The New York Times*, May 7, 2013. See also, John Campbell and Asch Harwood, "What's Behind Nigeria's Escalating Bodycount?" *The Atlantic*, May 21, 2013.

[38] "Freedom in the World Report, Burkina Faso," Freedom House, 2013.

[39] "Military Barracks in Disrepair Despite N12 Billion 2012 Budget," *Daily Trust*, March 18, 2013, available at <http://allafrica.com/stories/201303181685.html>.

[40] *Government Defence Anti-Corruption Index 2013* (London: Transparency International UK Defence and Security Programme, 2013).

[41] *Bribery in Public Procurement: Methods, Actors and Counter-Measures* (Paris: OECD, 2007), 47.

[42] Herbert M. Howe, *Ambiguous Order: Military Forces in African States*, (Boulder CO: Lynne Rienner Pub., 2005), 55.

[43] Ibid., 55.

[44] Rawings Otini, "Kenya Among Africa's Top Spenders on Military," *Business Daily*, November 1, 2012, available at <http://www.businessdailyafrica.com/Kenya-among-Africa-s-top-spenders-on-military-/-/539546/1609528/-/p833jtz/-/index.html>.

[45] Kwesi Aning, "Ghana," in *Parliamentary Oversight of the Security Sector in West Africa*, eds. Adedeji Ebo and Boubacar N'Diaye (Geneva: DCAF, 2008), 131.

[46] Toulabor, "Togo," 232.

[47] Wuyi Omitoogun and Eboe Hutchful, *Budgeting for the Military Sector in Africa: The Processes and Mechanisms of Control*, SIPRI (Oxford: Oxford University Press, 2006), 167.

[48] Daniel W. Henk and Martin Revayi Rupiya, *Funding Defense: Challenges of Buying Military Capability in Sub-Saharan Africa* (Carlysle: Strategic Studies Institute (SSI), September 2001), 19.

[49] Laurent Touchard, "Les 7 Péchés Capitaux," *Jeune Afrique* No. 2709 (December 9-15, 2012), 30.

[50] "The Rise and Rise of Museveni's Son – Brigadier Muhoozi Kainerugaba," *Wavuti.com*, August 29, 2012, available at <http://wavuti.weebly.com/news-blog/the-rise-and-rise-of-musevenis-son-brigadier-muhoozi-kainerugaba#axzz35fHd31tE>.

[51] Augustus Vogel, *Navies versus Coast Guards: Defining the Roles of African Maritime Security Forces*, ACSS Security Brief No. 2 (Washington DC: National Defense University Press, December 2009), 3.

[52] Leon Engelbrecht, "African Navies Declining," defenseWeb, January 20, 2010, available at <http://www.defenceweb.co.za/index.php?option=com_content&view=article&id=6204:african-navies-declining-&catid=51:Sea&Itemid=106>.

[53] Patrick Smith, "Africa's Armies: Facing Down Disorder," *The Africa Report* No. 49 (April 2013), 25.

[54] "Building Integrity and Countering Corruption in Defence & Security: 20 Practical Reforms," Transparency International (February 2011), 12.

[55] Adam Nossiter, "The Whiff of Conflict Grows in Mali," *The New York Times*, October 24, 2012.

[56] Jeffrey Gettleman, "The World's Worst War," *The New York Times*, December 25, 2012.

[57] Davin O'Regan and Peter Thompson, *Advancing Stability and Reconciliation in Guinea-Bissau: Lessons from Africa's First Narco-State*, ACSS Special Report No. 2 (Washington DC: National Defense University Press, June 2013).

[58] Wolfram Lacher, *Organized Crime and Conflict in the Sahel-Sahara Region*, The Carnegie Papers (Washington, DC: Carnegie Endowment for International Peace, September 2012).

[59] Ibid.

[60] Andrew Lebovich, "Mali's Bad Trip: 'Air Cocaine,' Al-Qaeda, and West African Drug Trade," *Foreign Policy*, March 15, 2013.

[61] Andrew Cottey, Timothy Edmunds, and Anthony Forster, "The Second Generation Problematic: Rethinking Democracy and Civil-Military Relations," *Armed Forces & Society* 29, No. 1 (Sep. 2002), 34 (citing Stanisław Andrzejewski, 1954).

[62] Helmoed Heitman, *Optimizing Africa's Security Force Structures*, ACSS Africa Security Brief No. 13 (Washington DC: National Defense University Press, May 2011).

[63] Khabele Matlosa, "From a destabilizing factor to a depoliticized and professional force: the military in Lesotho," in *Evolutions & and Revolutions: A Contemporary History of Militaries in Southern Africa*, ed. Martin Rupiya (Pretoria: Institute for Security Studies, 2005), 85-110.

[64] Barany, *Soldier and the Changing State*, 355-356.

[65] Ghana Armed Forces Internal Operations, Ghana Armed Forces website, available at <http://www.gaf.mil.gh/index.php?option=com_content&view=article&id=546:ghana-armed-forces-internal-operations&catid=42:army>.

[66] Kwame Asare Boadu, "Forestry Commission Inaugurates Armed Forest Guards," *Daily Graphic*, April 3, 2012, available at <http://www.modernghana.com/news/387087/1/forestry-commission-inaugurates-armed-forest-guard.html>.

[67] "Senegal's Armée-Nation: Lessons Learned from an Indigenous Model for Building Peace, Stability and Effective Civil-Military Relations in West Africa," Partners for Democratic Change, available at <http://www.partnersglobal.org/where/africa/senegal/Senegals Armee Nation.pdf/at_download/file>.

[68] Narcís Serra, *The Military Transition: Democratic Reform of the Armed Forces*, tr. by Peter Bush (Cambridge: Cambridge University Press, 2010) 86.

[69] Barany, *Soldier and the Changing State*, 356.

[70] Heitman, *Optimizing Africa's Security Force Structures*, 3.

[71] Barany, *Soldier and the Changing State*, 326.

[72] Abel Esterhuyse, "Educating for Professionalism: A New Military for a New South Africa," *South African Journal of Military Studies* 34, No. 2 (2006), 25.

[73] Samii, "Perils or Promise of Ethnic Integration?" 558-573.

[74] Liza E.A. Briggs, "Civilian and Enlisted Perspectives on the Armed Forces of Liberia (AFL): A Qualitative Research Study Report," AFRICOM Directorate of Intelligence and Knowledge Development (October 2010).

[75] "Building Integrity and Countering Corruption," 2011, 24.

[76] Mindia Vashakmadze, *Guidebook: Understanding Military Justice* (Geneva: Geneva Centre for the Democratic Control of Armed Forces (DCAF), 2010), 9. *Military Justice Legislation Model, Republic of South Africa, Military Discipline Supplementary Measures Act*, 1999 (Geneva: Geneva Centre for the Democratic Control of Armed Forces (DCAF), 2010).

[77] Barany, *Soldier and the Changing State*, 350.

[78] Matlosa, 2005, 85-110.

[79] Esterhuyse, "Educating for Professionalism," 25.

[80] Matlosa, 2005, 87.

[81] "President Signs Freedom of Information Law," International Freedom of Expression Exchange Clearing House, October 6, 2010.

[82] Briggs, "Civilian and Enlisted Perspectives".

[83] Ibid., 12.

[84] Mohamed Yahya Ould Abdel Wedoud, "Mauritania Decriminalises Press Offences," Magharebia, July 1, 2011, available at <http://magharebia.com/en_GB/articles/awi/features/2011/07/01/feature-03>.

[85] "Reality of the Freedom of Information Act," *Daily Trust*, September 17, 2012, available at <http://allafrica.com/stories/201209170161.html>.

[86] Raymond Louw, "Protection of State Information Bill Passed by South African Parliament," IPI, May 3, 2013, available at <http://www.freemedia.at/home/singleview/article/ipi-feature-protection-of-state-information-bill-passed-by-south-africa-parliament.html>. David Smith, "South Africa Secrecy Law Surprise as Zuma Rejects Controversial Bill," *The Guardian*, September 12, 2013.

[87] Arne Willy Dahl, "International Trends in Military Justice," (presentation at the Global Military Appellate Seminar at Yale Law School, New Haven, CT, April 1-2, 2011), available at <www.law.yale.edu/2011-04_International_trends.pdf>.

[88] Danielle Skinner, "Armed Forces of Liberia's Military Justice System Focuses on Human Rights and Discipline," US AFRICOM, May 16, 2011, available at <http://www.africom.mil/Newsroom/Article/8319/armed-forces-of-liberias-military-justice-system-f>.

[89] "Building Integrity and Countering Corruption," 2011, 22.

[90] Ibid., 33.

[91] "Military Ombudsmen," Backgrounder: Security Sector Governance and Reform Series (Geneva: DCAF, March 2006).

[92] Ben Magahy, Dominic Scott, and Mark Pyman, *Defence Corruption Risk in Sub-Saharan Africa: An Analysis of Data Relating Corruption in Defence Establishments to Development Outcomes* (London: Transparency International, 2009), 26 (citing Gupta, et al., 2000:15).

# ስለ ጸሃፊው

ኤሚል ኡድራጎ በቡርኪና ፋሶ እና በኢኮዋስ ፓርላማ በአቡጃ ናይጄሪያ የፓርላማ አባል ነው፡፡ ቀድሞም፣ በቡርኪና ፋሶ የሃገር ደህንነት ሚኒስቴር ከ 2008 እስከ 2011 አገልግሎዋል፡፡ ከቡርኪና ፋሶ የታጠቁ ሃይሎችም ኮሎኔል ሆኖ ሲያገለግል በጦር ተዋጊ ኮርፕስ እና በስለላ ስራ አገልግሎዋል፡፡ በአገልግሎቱ ጊዜም፣ ብዙ ሽልማቶችንም ሲቀበል፣ ይህም የወታደር የክብር ሜዳል እና የፖሊስ ክብር ሜዳል ሲሸለም እንዲሁም በተለያዩ የስልጠና ኮርሶች በካናዳ፣ ጋና፣ ፈረንሳይ፣ ማሊ፣ ናይጄሪያ፣ ራሻ፣ እና ዩናይትድ ስቴተስ ወስዶዋል፡፡ በተጨማሪም ዩኒፎርም ለብሶ በዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ኦፍ ኮንጎ የዩኤን ሰላም አስከባሪ አገልግሎዋል፡፡ በአለም አቀፍ ግንኙነት የፒኤች ዲ ዲግሪ ከስትራቴጂክ እና ዲፕሎማቲክ ጥናቶች ማእከል (ሲኢዲኤስ) በፓሪስ፣ ፈረንሳይ ተቀብሎዋል፡፡

**AFRICA CENTER FOR STRATEGIC STUDIES**
Director: Kate Almquist Knopf
National Defense University
300 Fifth Avenue, Building 20
Fort Lesley J. McNair
Washington, D.C. 20319-5066
Phone: +1 202 685 7300
Web site: www.africacenter.org

**AFRICA CENTER RESEARCH PAPERS**
Director of Research: Joseph Siegle, Ph.D.
Phone: +1 202 685 6808
Email: Sieglej@ndu.edu

AFRICA CENTER FOR STRATEGIC STUDIES
CENTRE D'ETUDES STRATEGIQUES DE L'AFRIQUE
NATIONAL DEFENSE UNIVERSITY